# ሽግግሩ ከአንዱ የመከራ አዙሪት ወጥተን በአይነቱ ልዩ ወደሆነ ሌላ የመከራ አዙሪት የምንዘፈቅበት ወይንስ ከታሪካዊ ችግሮቻችን የምንገላገልበት?

## አቻምየለህ ታምሩ

*ይህ ጽሁፍ Vision Ethiopia October 22, 2016 እ.ም. ባዘጋጀው ጉባዔ ላይ በሰዓት እጥረት ምክንያት በከፊል ብቻ የቀረበው ጽሁፍ ሙሉ ዘገባ ወይንም ሀተታ ነው።*

## 1. መግቢያ

ይህ ጽሁፍ ወድቃ በምትገኘው ኢትዮጵያ የመጣንባቸው ያለፉት አርባ ሁለት የመከራ አመታት የት እንዳደረሱን በከፊል በመቃኘት ወደፊት እየታሰበ ባለው ሽግግር የመንግስት ለውጥ ብቻ ሳይሆን የስርዓትም ለውጥ ይመጣ ዘንድ ልንመሰረትባቸው የሚገቡ መሰረታውያን [fundamentals] እና ሊካተቱ የሚገባቸው ቁም ነገሮች ምን መሆን እንዳለባቸው እንደ አንድ የአማራ ድምጽ የሚሰማኝንና የሚታየኝን የገለጽኩበት ነው።

ጽሁፌ የሚጀምረው በግራ ፖለቲካ ልክፍት ተንጋደው የበቀሉት የአገራችን የዘር ፖለቲከኞችና የፕሮፓጋንዳ ጸሀፊዎች የደረቷቸውና እኛ እንደ እውነተኛ ታሪክ ቆጥረን ሳንመረምር የተቀበልናቸውን የተከደኑ የፖለቲካ ድርሰቶች [manufactured and distorted stories] ከፍቶ በማየት ፍንትው ብሎ የሚታየውን ነባራዊ እውነታ በግልጽ ተንትኖ በማቅረብ ነው። ከዚያ በመቀጠል እነዚህ ድርሰቶች የወለዱት ፖለቲካ በተለየ መልኩ በአማራ ላይ ያስከተለውን ግፍና በደል ተተኪው ትውልድ ይፋረድበት ዘንድ የኢትዮጵያ አለት፣ ተራራ፣ አፈርና ቅጠል በታሪክ መዝገብነት ከትቦ ካስቀመጠው የዶሴ ክምር በማንካ በመጨለፍ ባለፉት ሀያ አምስት አመታት ውስጥ ብቻ በአማራ ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ፍጅት አይነትና ይዘት ለማቅረብ እሞክራለሁ።

በመጨረሻም ወደፊት እንድትኖረን በምንፈልጋት ኢትዮጵያ ተመሳሳይ አዙሪት ውስጥ እንዳንዘፈቅና የመንግስትም የስርዓትም ለውጥ እንድናካሂድ ከጥግ እስከ ጥግ ልናደርጋቸው ከሚገቡ ተግባራት መካከል የተወሰኑትን በማውሳትና በሽግግሩ ሂደት መካተት የሚገባቸውን ጉዳዮች በማቅረብ ጽሁፌን አጠቃልላለሁ።

## 2. ሳንመረምር የተቀበልናቸው የግራ ፖለቲካ የፈጠራ ድርሰቶች

በኢትዮጵያ የሶስት ሺህ አመታት ጉዞ ውስጥ እንዳለፉት አርባ ሁለት አመታት በጥላቻና በሀሰት ላይ የተመሰረቱ የፈጠራ ታሪኮችና የፖለቲካ ልብወለዶች እንዳሸን የፈሉበት ዘመን ኖሮ አያውቅም። ማተባቸውን የበጠሱት የአገራችን የግራ ፖለቲካ የፕሮፓጋንዳ ጸሀፊዎች በተለይም ከኢትዮጵያና ከአማራ አንጻር ያልፈጠሩት የፖለቲካ ታሪክና ያልመሰረቱት የሀጢዓት ክስ የለም።

ከዛሬ አርባ ሁለት አመታት በፊት በመሳሪያ ኃይል ወደ ስልጣን የመጣው ደርግ ለኢትዮጵያ ህዝብ ያተስተጋባው ፕሮፓጋንዳ የቁልቁለቱ መንገድ መጀመሪያ ነው። ለአስራ ሰባት አመታት ንጉሰ ነገስ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ በተነዛው ፕሮፓጋንዳ ንጉሰ ነገስቱ ከአልጋ ወራሽነታቸው ጀምሮ ለሀምሳ ስምንት አመታት ሙሉ በስልጣን በቆዩበት ዘመን ውስጥ የኢትዮጵያን ህዝብ ሙብት ገፈው ሲጨቁኑና ሲያሰቃዩ ከመኖር በስተቀር አንዳችም ቁም ነገር ሰርተው እንደማያውቁ አዲስ የፖለቲካ ታሪክ ተጻፈ። በዚህ አዲስ ታሪክ አዕምሮው የተመረዘ ሁለት ትውልድ ተፈጠረ። ከላይ ያሉት ደም የጠማቸው የደርግ ባለሥልጣናት በየደረጃው ከበታቻቸው አስቀምጠዋቸው የነበሩት ተካታዮቻቸው የበላዮቻቸው የባህሪ ታናሽ ወንድም የሆኑ ገዳዮች ስለነበሩ በተዘረጉ የመንግስት ተቋማት ሁሉ፡ ሁሉ ነገር እየቆረቆዘ፣ የሞራልና የሥነ ምግባር እሴቶች ደብዛቸው እየጠፋ፣ ትርጉሙ ምን እንደሆን የማይታወቅ አምልኮተ ህብረተሰባዊነት በመንግስትነት ተሰይሞ፣ ጥሩንባ እየነፋ የሚገድል፣ ህዝብን ወደ ከብትነትና አልፎም ወደ ግዑዝ ድንጋይነት የሚለውጥ ሰይጣናዊ የመንግስት አመራር ተተከለ። ከወደቀ ሀያ አምስት አመታት የሆነውን አገዛዝ ከዚህ በላይ አልወቅሰውም።

ትላልቆቹ ባለጌዎች ወታደሮቹ ደርጎች ተወግደው ትናንሾቹ የትግራይ ሽፍቶች ወያኔዎች የሻዕብያ ጀሌ ሆነው አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ደርግ መጥፋት አለባቸው በሚላቸው መደቦች ላይ ይወስዳቸው የነበሩ አብዮታዊ እርምጃዎችን ሁሉ በአማራ ላይ በጅምላ መፈጸም ጀመሩ። አማራ ገዢና በዳይ ነበር፤ አማራ የመሬት ከበርቴ ነበር፤ በድሮ ስርዓት ብሔር ብሔረሰቦች የትምህርት እድል ተነፍገዋል፤ ሙስሊሞች እንዲማሩም ሆነ በየመስሪያ ቤቱ እንዲቀጠር አይፈቀድላቸውም ነበር፤ ወዘተ. . . የሚሉ የፈጠራ ታሪኮች በየፖለቲካ ፓርቲውና በየጉራንጉሩ መደስኮር ጀመሩ። እነዚህ የፖለቲካ ታሪኮችና የሀጢዓት ክሶች ባለፉት ሀያ አምስት አመታት በአማራ ላይ ለተፈጸሙት ግፍና በደሎች መንገድ ጠራጊዎች ናቸው። በመላው ዓለም የዘር ማጥፋት የተካሄደባቸው ህዝቦች ሁሉ የጥቃት ሰለባ ከመሆናቸው በፊት ልክ በአማራው ላይ ባለፉት አርባ ሁለት አመታት እንደተካሄደው አይነት በአብዛኛው በቀጥታ፤ አንዳንዴ ደግሞ በኮድ ስም የተፈረጁና

ጥላሸት የተቀቡ [demonize የተደረጉ] ነበሩ። አማራ ገዢና በዳይ ነበር፤ አማራ የመሬት ከበርቴ ነበር፤ የአማራ መንግስታት ብሔር ብሔረሰቦችን የትምህርት እድል ነፍገዋል፤ የአማራ ገዢ መደብ ጨቋኝና አጥፊ ነበር፤ ወዘተ የሚሉት ፍረጃዎችና ስም ማጥፋቶች በአማራ ላይ ለተፈጸመው ጥቃት መጀመሪያዎች ናቸው። እነዚህ ፍረጃዎችና የስም ማጥፋቶች «አጥፊ የነበረው መጥፋት አለበት» ለሚለው አስተሳሰብ የርዕዮተ አለም ጡንቻ የሚሆኑ ናቸው። ወረድ ብዬ ከነዚህ ሳንመረምር የተቀበልናቸው የፖለቲካ ታሪኮችና የሀጢዓት ክሶች መካከል የተወሰኑትን በማንሳት ከታሪክ አኳያ እውነታው ምን እንደነበር ማሳየት እፈልጋለሁ።

## 2.1 «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበርን»?

አቶ ጁኔይዲ ሳዶን ሁላችሁ ታውቋቸዋላችሁ። ከአንድ ወር በፊት ከተወዳጁ ጋዜጠኛ ከሲሳይ አጌና ጋር በኢሳት ቴሌቭዥን ቃለ ምልልስ ባደረጉበት ወቅት «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» ሲሉ በድፍረት ተናግረዋል። ይህ የአቶ ጁኔይዲ አስተያየት የኦነግም የርዕዮተ አለም መሰረት ነው። ብዙ ሰው የዚህ ፍጹም የተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ እንደሆነ ባስብም ላለፉት ጥቂት አመታት የጥሞና ጊዜ ያገኙት አቶ ጁኔይዲ ግን እስከዛሬ ድረስ ይህንን የተሳሳተ አስተሳሰብ አለማረማቸው ሳይገርመኝ አልቀረም። እስቲ ዶሴው ይውጣና እውነታው ምን ይመስል እንደነበር ይታይ።

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ታሪክ ተማሪዎች በመንግስት ተመርጠው ወደ ውጭ አገር በመላክ ምዕራባዊ ወይንም አውሮፓዊ ትምህርት [ዘመናዊ ትምህርት ላለማለት ነው] እንዲቀስሙ የተደረገው በ1913 ዓ.ም. በንግስተ ነገስት ዘውዲቱና በአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮነን ዘመን ነበር። በ1913 ዓ.ም. ለመጀመሪያ የምዕራብ ትምህርት እንዲቀስሙ የተላኩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቁጥር ሶስት ነበር። ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ «Pioneers Of Change In Ethiopia: Reformist Intellectuals Of Early Twentieth Century» በሚል እ.ኤ.አ. በ2002 አ.ም. ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ እንዳሰፈሩት ሶስቱ ተማሪዎች መላኩ በያን [ኋላ ዶክተር] ፣ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድና ወርቁ ጎበና ናቸው።[1] ከነዚህ ሶስት ግንባር ቀደም የምዕራብ ትምህርት እንዲማሩ ከተላኩ የኢትዮጵያ ተማሪዎች መካከል በብሔረሰብ መመዘኛ ሁለቱ ማለትም መላኩ በያንና ወርቁ ጎበና ኦሮሞዎች ናቸው።

---

[1] *Bahru Zewde Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century. Athens: Ohio University Press, 2002. PP. 89-90*

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፤ "የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ" በሚል በጻፉት የታሪክ መጽሀፍ ውስጥ እነዚህ ሶስት ወጣቶ በመጀመሪያ ህንድ ሄደው ስላልተስማማቸው ወደ አሜሪካ እንደተዛወሩ አስፍረዋል። አሜሪካም እንደደረሱም 29ኛው የአሜሪካ ፕሬዝደንት የሆኑት ዋረን ሃርዲንግን አቀባበል አድርገውላቸዋል። ፕሬዝደንቱ ፊት ቀርበውም ከልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮነን የተላከውን ደብዳቤ አድርሰዋል። ፕሬዝደንቱም ደብዳቤውን ገልጠው ካነበቡ በኋላ የልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮነንን ኢትዮጵያውያንን ጥራት ያለው ትምህርት የማስረማር ፍላጎት በመረዳታቸው ወጣቶቹ እነ መላኩ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ፕሬዝደንቱ ራሳቸው በተማሩበት ኦሃዮ በሚገኘው ማሪታ ኮሌጅ ውስጥ ገብተው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ስለመከሯቸው ወደ ኦሃዮ አቅንተው የአሜሪካ ትምህርታቸውን በማሪታ ኮሌጅ ተከታትለዋል።

መላኩ በያን የኦሃዮ ትምህርቱን አጠናቆ ወደ ዋሽንግተን ዲሲ በማምራት በሕክምና ትምህርት ከሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ወደ አገሩ ሊያቀና ሲል ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በመውረሯ እዚያው አሜሪካ በመቆየት ለኢትዮጵያ አርበኞች እርዳታ በተለይም ከጥቁር አሜሪካኖች የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማሰባሰብ የኢትዮጵያን ጀግኖች አቅም ያጎለበተ አርበኛ ነበር። በመጨረሻም የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ቀንዲልና ብቸኛ ተስፋ የኾነችው ኢትዮጵያ በፋሽሽት ጥሊያን መወረር ዕረፍት ከነሳውና የኢትዮጵያን አየር ኃይል አርበኞች በመቀላለቀል በተለያዩ ግንባሮች ለኢትዮጵያውያን የነጻነት ተጋድሎ ዋና አጋር ለመኾን ከበቃው እውቁ ጥቁር አሜሪካዊው አርበኛ ኮ/ል ጆን ሮቢሰን ጋር በመሆን እ.ኤ.አ. 1936 ኢ.ም. አሜሪካን ለቅቆ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በኦጋዴን ግንባር ከጥቁር አንበሳ አርበኞች ጋር አብሮ ሲዋጋ ቆይቶ አዲስ አበባ በፋሽስት ጥሊያን ቁጥጥር ስር ስትወድቅ መጀመሪያ ወደ እንግሊዝ በመሸሽ፤ ከዚያም ወደ አሜሪካ በመሻገር ለኢትዮጵያ አርበኞች እርዳታ ገንዘብና ቁሳቁስ በማሰባሰብ ላይ ሳለ በኒሙኒያ በሽታ ታሞ እ.ኤ.አ. በ1940 ዓ.ም. ከዚህ አለም በሞት እንደተለየ ዮሹዋ እስራኤል የተባለ አፍሪካ አሜሪካዊ ምሁርና የታሪክ ተመራማሪ «The Lion and the Condor: The Untold Story of Col. John Robinson and the Crippling of Ethiopia» በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ በሰፊው ተርኮታል። በሻህ ወረድም ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ አገሩን በታላቅ ቅንነትና ችሎታ አገልግሏል። በ1929 ዓ.ም. ግራዚያኒን ለመግደል ሙከራ በተደረገ ጊዜ ተገድሏል።

እነ መላኩ ከተላኩ ከሁለት ዓመት በኋላ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኮነን ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ውጭ አገር ለከፍተኛ ትምህርት 33 የሚሆኑ ተማሪዎችም ተልከው

ነበር። ከነዚህ ተማሪዎች መካከል ሙስሊም የሆኑ መሀመድ ማህዲና ከሊል ማህዲ የሚባሉ ተማሪዎች ይገኙበታል። ከሰላሳ ሶስቱ ተማሪዎች በብሔረሰብ መመዘኛ በቁጥር የሚልቁቱ ኦሮሞዎች ሲሆኑ ብዙ ሰው የሚያውቃቸው እነ ወልደ ኪዳን በያን፣ ወዳጆ ኢካ፣ ዮሐንስ ቦሩ፣ ገብረየሱስ ጉቱ፣ ተክለ ብርሀን ጉሩሙ፣ ገብረ ማርያም አመንቴና አበራ ደገፉ ይገኙበታል።[2]

ቀጣዩና የአቶ ጁይኔዲን «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» የሚለው ክስ መሰረት እንደሌለው የሚያስረግጥልን ዋነኛ ማስረጃ ደግሞ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ማብቂያ ማለትም እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች የተሰሩት የትምህርት ቤቶች ቁጥር ነው።

ከ1966 ዓ.ም. በፊት በየጠቅላይ ግዛቱ የነበሩ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር ከማቅረቤ በፊት የኢትዮጵያን ምዕራባዊ ትምህርት ታሪክ በከፊል ላውሳ። ብዙ ሰው የኢትዮጵያን መደበኛ የሆነ ምዕራባዊ ትምህርት ጅማሮ ታሪክ የሚያያይዘው በአዲስ አበባ ከተማ ከተቋቋመውና ዛሬም ድረስ ካለው አንጋፋው የዳግማዊ ምኒሊክ ትምህርት ቤት ጋር ነው። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ምዕራባዊ ትምህርት የበቀለው ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ከመቋቋሙ ከስድሳ ሦስት ዓመታት በፊት ማለትም ከዛሬ 170 አመታት በፊት ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን በኩል 903 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትግራይ እንደርታ ወረዳ ለዓዲግራት ከተማ ቅርብ በሆነች ጎልዓ የተባለች መንደር ውስጥ የተመሰረተው ላዛርስት ሚሲዮን የካቶሊክ ትምህርት ቤት ነው። ይህ ትምህርት ቤት የተከፈተው በታኅሣሥ 1837 ዓ.ም. ነው። ትምህርት ቤቱ ስራ ሲጀመር ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ አምስት መምህራን የነበሩት ሲሆን ትምህርት መስጠት የጀመረው 13 ወንድ ተማሪዎች በመቀበል ነበር። በትምህርት ቤቱ ይሰጡ ከነበሩ የትምህርት ዓይነቶች መካከል ግእዝ፣ አማርኛ፣ ላቲን፣ ቲኦሎጂና ሥነ ቅርፅ የሚገኙበት ሲሆን፤ የማስተማሪያ ቋንቋው በአብዛኛው አማርኛ ነበር[3]።

ልበ በሉ! ይህ ትግራይ አዲግራት ውስጥ ከዛሬ 170 አመታት በፊት የተከፈተው ቀዳሚው የኢትዮጵያ ምዕራባዊ ትምህርት ቤት በአማርኛ ስራ የጀመረው፤ «አማርኛን ጫኑብን» እየተባሉ የሚወገዙት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ከመወለዳቸው ከአንድ አመት በፊት ነበር። የዚያ ዘመን የትግራይ ተማሪዎች አማርኛ ይናገሩና ይማሩ የነበሩት ማዕከላዊ መንግስት በፈረሰበት በዘመነ መሳፍንት

---

[2] *መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፤ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣1999፡ ገጽ 325 -327*

[3] http://aigaforum.com/article1/Guola-the-door-modern-scholar.pdf

ዘመን ማንም ሳይጭንባቸው ነበር። ከዚህ ትምህርት ቤት በኋላ በመላው ኢትዮጵያ የተከፈቱት ትምህርት ቤቶች ይሰጧቸው የነበሩት የትምህርት አይነቶች ተመሳሳይ ነበሩ።[4] ሆኖ ግን አማርኛ ተጫነብን ተብሎ ትልቅ ፖለቲካ የሆነው ቀደም ብዬ ያቀረብሁት በዘመነ መሳፍንት ዘመን ትግራይ ውስጥ ተጀመሮ ኋላ ላይ በመላው ኢትዮጵያ እየተስፋፋ በመጣነው የትምህርት ስርዓት የተነሳ ነበር። ከዚህ እውነት ተነስተን «አማርኛ በግድ ተጫነብን» የሚለው የፈጠራ ክስ ምን ያህል ውሀ የማይቋጥር ፕሮፓጋንዳ እንደሆነ መገንዘብ እንችላለን።

ሁለተኛ የኢትዮጵያ መደበኛ ትምህርት ቤት በ1898 ዓ.ም. በሀረር ከተማ የተከፈተው የራስ መኮነን የመጀመሪያ ትምህርት ቤት ሲሆን በሶስተኛነት የተከፈተው ትምህርት ቤት ደግሞ በ1900 ዓ.ም. የተከፈተው ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ነው። ከዚህ በመቀጠል በአራተኛነት የተከፈተው በ1917 ዓ.ም. ስራ የጀመረው ተፈሪ መኮነን ትምህርት ቤት ነው። አምስተኛው የኢትዮጵያ መደበኛ ትምህርት ቤት ደግሞ በዚያው ዓመት ማለትም በ1917 ዓ.ም. በወሊጋ የተከፈተው የደጃዝማች ገብረእግዚያብሔር ትምህርት ቤት ነበር። ከዚህ ትምህርት ቤት በሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ለ2ኛና ለ3ኛ ክፍል ይመጥናሉ የተባሉ 23 የወሊጋ ልጆች ወደ አዲስ አበባ ተልከው ተፈሪ መኮነን ትምህርት ቤት በ1918 ዓ.ም. በአዳሪነት ገቡ።[5] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ እንደጻፉት አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮነን "ካገራችን ወጣን፣ ከዘመድ ተለየን የማለት ኃሳብ አይግባችሁ፤ በሚቻለንን ሁሉ እናት አባት ሆነን እንጠብቃችኋለን" በማለት ለተማሪዎቹ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

አሁን ቀደም ብዬ ወዳነሳሁትና የተለመደው ስህተት ይታረም ዘንድ እውነቱን ወደሚያሳየን አሀዛዊ ማስረጃ ወደማቅረቡ ልሻገር። የማቀርበው አሀዛዊ ማስረጃ ምንጭ ማንም ሰው የሚያገኘውና «Ethiopia: A country study» በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ1991ዓ.ም. በThomas P. Ofcansky & LaVerle Berry አርታዒነት Library of Congress Federal Research Division ያሳተመው የምርምር handbook series ገጽ 336 ላይ የተገኘ የጥናት ውጤት ነው። በዚህ የጥናት ውጤት መሰረት በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት መጨረሻ ላይ ዛሬ ወያኔ አማራ ኦሮምያ ክልል ብሎ በፈጠራቸው የአስተዳደር ክልሎች ውስጥ ይገኙ የነበሩ የትምህርት ቤቶችን ቁጥር የሚከተለውን ይመስላል።

---

[4] *መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፤ የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፣1999፡ ገጽ 325 -327*
[5] *Ibid*

**ሰንጠረዥ ፲፡- በኢትዮጵያ የተለያዩ ጠቅላይ ግዛቶች በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በ1966 ዓ.ም. የነበሩ ትምህርት ቤቶች ብዛት[6]**

| ጠቅላይ ግዛት | 1966 ዓ.ም. | | |
|---|---|---|---|
| | ክፍል [1-6] | ክፍል [7-8] | ክፍል [9-12] |
| አርሲ | 135 | 19 | 3 |
| ባሌ | 83 | 8 | 1 |
| ኤርትራ | 428 | 66 | 14 |
| ጋሞጎፋ | 77 | 8 | 3 |
| ጎጃም | 135 | 14 | 4 |
| ጎንደር | 184 | 21 | 4 |
| ሐረርጌ | 214 | 47 | 7 |
| ኢሉባቦር | 137 | 14 | 4 |
| ከፋ | 93 | 11 | 3 |
| ሲዳሞ | 148 | 31 | 6 |
| ትግራይ | 178 | 19 | 7 |
| ወለጋ | 463 | 28 | 10 |
| ወሎ | 158 | 23 | 3 |

«ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ወለጋ በቁጥር 463 የሚሆኑ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበሯት። «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር» በተባሉት በጎጃም 135፣ በጎንደር 184 እና በወሎ 158 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። ይህ ማለት «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበሩ» በተባሉት በጎጃም፣ በጎንደርና በወሎ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የተሰሩት ትምህርት ቤቶች በአንድ ላይ ተደምረው ወለጋ ብቻዋን ከነባሯት ጋር ተቀራራቢ ነው። «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር

[6] *Washington, D.C. : Federal Research Division, Library of Congress : For sale by the Supt. of Docs., U.S. G.P.O., 1993. PP. 336.*

ተደርጎ ነበር» በተባለበት  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት   ሀገርጌ 214 አንደኛ ትምህርት ቤቶች ነበሯት። እንደ ወለጋ ሁሉ ሐረርጌ የነበራት የአንደኛ ደረጃ  ትምህርት ቤቶች ቁጥር ጎጃም፣ ጎንደርና ወሎ እያንዳንዳቸው ከነበሯቸው በላይ  ነው።

በቀ.ኃ.ሥ.  ዘመን መጨረሻ ዛሬ ኦሮምያ በሚባለው ክልል ውስጥ ሸዋን ሳይጨምር  ባጠቃላይ 1180 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር» በሚባለው  ዛሬ ወያኔ የአማራ ክልል እያለ በሚጠራው ክልል ውስጥ  ደግሞ [ይሄም ሸዋን ሳይጨምር ነው]  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት   477  የአንደኛ ደረጃ  ትምህርት ቤቶች ነበሩ። ይህ ማለት ኦሮምያ የሚባለው  ክልል በቀ.ኃ.ሥ.  የነበሩት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር  አማራ የሚባለው ክልል  በዚያ ዘመን ከነበሩት  ከሁለት  እጥፍ  በላይ  ነው ማለት ነው።

ከሰባኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ትምህርት ይሰጥባቸው የነበሩ የትምህርት ቤቶችን ቁጥር ካየን ደግሞ «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት አቶ ጁኔይዲ የተወለዱባት አርሲ  19 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሯት፤  ጎጃም ግን   14 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሯት።  በተመሳሳይ ዘመን  ሀረርጌ 47 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ሲኖሯት፤ ጎንደር  ደግሞ   21 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሯት።  «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ወለጋ  28 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ሲኖሯት፤ «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር»  የተባለው ወሎ  ግን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት 23 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሯት።

ዛሬ ኦሮምያ በሚባለው ክልል ውስጥ ሸዋን ሳይጨምር «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት   147 ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር» በሚባለው  ዛሬ ወያኔ የአማራ ክልል እያለ በሚጠራው ክልል ውስጥ  ደግሞ [ይሄም ሸዋን ሳይጨምር ነው] በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት   58   ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሩ።

ከዘጠኝ እስከ  አስራ ሁለተኛ  ክፍል ድረስ ትምህርት ይሰጥባቸው የነበሩ የትምህርት ቤቶችን ቁጥርም ስናይ «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ሀረርጌ 7 ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ሲኖሯት፤ «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር»  የተባለው ጎንደር  ግን  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት 4 ብቻ  ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሯት።  «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ወለጋ  10  ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ሲኖሯት፤ «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር»  የተባለው ወሎ  ግን  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት 3 ብቻ  ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሯት።

በድምር ስናየው  ዛሬ ኦሮምያ በሚባለው ክልል ውስጥ ሸዋን ሳይጨምር «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» በተባለበት  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት   26  ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ  ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ  «በነፍጠኛው ስርዓት ተጠቀሚ ነበር» በሚባለው  ዛሬ ወያኔ የአማራ ክልል እያለ በሚጠራው ክልል ውስጥ  ደግሞ [ይሄም ሸዋን ሳይጨምር ነው]  በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት  11 ብቻ    ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ትምህርት  የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። ኦሮሞ እንዳይማር  ቢፈለግ  ኖሮ ኦሮሞው  መካከል በአማራው  መካከል ከተሰሩ ትምህርት ቤቶች ቁጥር  በእጥፍ የሚበልጡ ትምህርት ቤት አይሰሩም ነበር። እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ  ኢትዮጵያ ውስጥ  ሁለት  ብቻ የአይነ ስውራን ማስተማሪያ ትምህርት ቤቶች ነበሩ።  እነዚህ ሁለት  ትምህርት ቤቶች የሚገኙት  ደምቢ ዶሎና  ሰበታ ነበር። አቶ ጁኔይዲ እንደሚሉት  ኦሮሞ እንዳይማር ቢፈለግ  ኖሮ ደምቢ ዶሎና ሰበታ መርሀ እውራን ትምህርት ቤቶች አይከፈቱም  ነበር።

ንጽጽሩን ከህዝብ ቁጥር ጋር የበለጠ ማመሳከር  ትችሉ ዘንድ መረጃው በተሰበሰበበት በ1976 ዓ.ም. በተካሄደው የደርግ የህዝብና የቤት ቆጠራ መሰረት የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር 12, 387, 664 ሲሆን ከአማራ ህዝብ ቁጥር ደግሞ 12,055, 250 ነበር። ይህ ማለት መረጃው በተጠናቀረበት ወቅት በተካሄደው ብሔራዊ የቤትና የህዝብ ቆጠራ መሰረት  የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር ከአማራ ህዝብ ቁጥር የሚበልጠው በሶስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ አራት መቶ አስራ አራት [332, 414] ብቻ ነበር።

ይህ ማለት አቶ ጁኔይዲ «ባለፉት ስርዓቶች ኦሮሞ እንዳይማር ተደርጎ ነበር» ባሉበት ዘመን ከአማራ ህዝብ ቁጥር ጋር ተቀራራቢ የህዝብ ቁጥር የነበረው የኦሮሞ ህዝብ በትምህርት አቅርቦት ረገድ ከአማራ ህዝብ አንጻር ሲታይ ከሁለት እጥፍ በላይ ተጠቃሚ ነበር ማለት ነው። መሬት ላይ የነበረው እውነቱ ይሄ ሆኖ ሳለ፤ ከአማራ አንጻር ከሁለት እጥፍ በላይ ተጠቃሚ የነበረው ኦሮሞ በትምህርት ረገድ በተለየ መልኩ ተጎጂ እንደነበር ተደርጎ መቅረቡ ፍጹም ነውር፣ የተሳሳተና ከእዉነት የራቀ የዉሸት አባባል ነው።

እንግዲህ! ባለፉት አርባ ሁለት አመታት ፖለቲካ ሆኖ እዚህ ያደረሰን ይህና ተመሳሳይ የተሳሳቱ ክሶች የወለዱት የጥላቻ ፖለቲካ ነው። በዚህ ሆን ተብሎ በተፈጠረ የሀሰት ለረዥም ዓመታት ተጋብተውና ተዋልደው በአንድነት አገር ያቆሙት፤ የጋራ እሴቶችን የፈጠሩት፤ በጋራ አገራዊ ተቋማትን የገነቡት፤ ጠላት ሲመጣ አብረው የመከቱት የኦሮሞና የአማራ እንዲሁም የሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላማዊ ግንኙነት ታውኮና በአንድ ላይ መቆም የማይችሉ እሳትና ጭድ እንደሆኑ ተደረጎ ለማሳየት ተሞክሯል። በርግጥ ዛሬ ላይ የአማራና የኦሮሞ ልጆች በግራ ፖለቲከኞች የታጠረውን የጥላቻ ግንብ ደርምሰው ያንተ ደም የኔም ደም መባባል ጀምረዋል። ፕሮፌሰር ዶናልድ ሌቪን አሜሪካን አገር በሚኖሩ የኤርትራና የኢትዮጵያ ወጣቶች መካከል ተጀምሮ የነበረው መቀራረብ በሁለቱም ወገን የስድሳዎቹ የግራ ፖለቲካ አራማጆች ሲገቡበት እንደፈረሰ ሲናገሩ ሰምቻለሁ። በኦሮሞና በአማራ ወጣቶች መካከል ዛሬ እየተየ ያለው መቀራረብ የስድሳዎቹ የግራ ፖለቲከኞች በመሀል ገብተው የለመዱትን የጭቃ ጅራፍ ካላጮሁና ወጣቶቹም የጭቃ ጅራፍ እንዲወራወሩ ጥላቸውን ካላጠሉባቸው፤ የሁለቱ ህዝቦች ወጣቶችም ዛሬ ባላቸው የመተባበር ስሜት ላይ ከላይ የተጠቀሱትን አይነት ፍጹም ውሸትና ከፋፋይ የፈጠራ ታሪኮችን ቆም ብለው መርምረው ተገቢውን እርማት በማድረግ ሆድና ጀርባ ያደረጋቸውን የግራ ፖለቲካ ጭነት አራግፈው በእውነትና በወንድማማችነት ላይ በመመስረት ፍላጎቶቻቸውን አስተሳስረው በጣምራ መንቀሳቀስ ከቻሉ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ቀንድም ተስፋ ይሆናሉ የሚል እምነት አለኝ።

## 2.2 መሬት የማን ነበር? አሁንስ የማነው?

አማራውን የመሬት ከበርቴና የፊውዳል ምልክት አድርጎ ማቅረቡ ሌላው የግራ ፖለቲካ በአገራችን የጣለው ጠባሳ ነው። ይህም ጠባሳ አማራው ለተደጋጋሚ ጊዜ የጥቃት ማእከል እንዲሆን የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ ዘመቻ ዛሬም ድረስ አልቆመም። ከዚህ ጉባዔ በፊት በነበረው የቪዥን ኢትዮጵያ ጉባዔ ላይ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ በንጉሰ ነገስቱ ዘመን ነበረ ስለሚሉት የአማራ የመሬት

ከበርቴነት በድፍረት ሲናገሩ ሰምቻለሁ። የግራ ፖለቲካ ልክፍት ያጠላበቱ የኢትዮጵያ ስኮላርሺፐ ሁል ጊዜ ያሳዝነኛል። ካድሬ ያወራው የፈጠራ ክስ ምሁሩ ጋር ሲደርስ ከፍ ብሎ መመርመር ሲገባው ምሁሩ ፕሮፌሰር የካድሬውን ፕሮፓጋንዳ እየደገመ ያስተጋባል። ወጉ ግን የካድሬው ፕሮፓጋንዳ ምሁሩ ጋር ሲደርስ የታሪክ ሰዎች History has Records of Names, Dates ,Places and Reference to Sources **በሚሉት ተፈትኖ ከፍ ማለት ነበረበት።**

አማራው የመሬት ከበርቴነት ምልክት ተደርጎ የሚነሳዝ የግራ ፖለቲካ ርዕዮተ አለም አራማጆች ከጻፉት የፈጠራ ክስ በስተቀር መሬት ላይ የወረደ እውነትነት የለውም። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የነበረው የመሬት ከበርቴነት ደረጃ በብሔረሰብ ይመንዘር ከተባለ ፕሮፌሰር መሳይ ከበደ የደገሙት የወያኔ፣ የኦነግና የሌሎች የግራ ሀይሎች ፕሮፓጋንዳ ውሀ አይቋጥርም። ምሁራኖቻችን ሲናገሩና ሲጽፉ፤ እንደ ወረደ የሚቀበል እንጂ እያንዳንዷን ነገር በአንክሮ የሚከታተል፤ የሚመለከትንና የሚናገሩትንም ሆነ የሚጽፉትን ነገር የሚፈትሽ፤ መረጃና ማስረጃ አገላብጦ እውነቱን የሚያወጣና የሚሞግታቸው ሰው የሚኖር አይመስላቸውም።

ራስ መስፍን ስለሺን ሁላችሁም የምታውቋቸው ይመስለኛል። ራስ መስፍን የጦር አበጋዝ፤ በግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ስላሴ ዘመን መንግስት የሸዋ ጠቅላ ግዛት እንደራሴ እና በተለያዩ የመንግስት ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ለ54 ዓመታት ያገለገሉ የኦሮሞ ተወላጅ ናቸው። የራስ መስፍን ባለቤት የጃራ መስፍን እናትና የቁለሙ ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ የልጅ ልጅ የሆኑት ወይዘሮ የሺመቤት ጉማ ወለጋ ውስጥ ብቻ 500 ጋሻ መሬት ነበራቸው። በኢትዮጵያ ታሪክ ራስ መስፍን ስለሺን የሚያህል የመሬት ከበርቴ አይገኝም።[7] «አማራ የመሬት ከበርቴ ነበር» እየተባለ የሚቀርበውን መሰረተ ቢስ ፍረጃ ከራስ መስፍንና ከባለቤታቸው በተጨማሪ በየአካባቢው የነበሩትን ፈርጣማ የመሬት ከበርቴዎችን ዝርዝር ማቅረብ ይቻላል።[8] አነስተኛ ይዞታዎችን በሚመለከትም የባለቤትነት ዝርዝሩ ቢወጣ አማራው ከሌላው ህዝብ የበለጠ የመሬት ባለቤትነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መቅረብ አይችልም።

ከመሬት ጋር በተያያዘ ሌላው ማንሳት የምፈልገው ተጠየቅ የመሬት ለራሹን ጉዳይ ነው። የየካቲት 1966ቱን አብዮት ካፈነዱት ጥያቄዎች መካከል ዋነኛው የወቅቱ ተማሪዎች በመፈክርነት

---

[7] Africa Report, XX (May-June, 1974), p.33.

[8] *Political linkage: The relationship between education, western educated elites, and the fall of Haile Selassie's feudal regime: Milkias, Paulos Amays, McGill University, 1982. PP.410.*

አብዝተው ያሰሙት የነበረው «መሬት ላራሹ» የሚለው የመሬት አልባው ገበሬ የመብት ጥያቄ ነበር። በርግጥ «ከአብዮቱ» በኋላ በገቢር በይሆንም በስም ጭሰኛ የሚባል የህብረተሰብ ክፍል ጠፍቷል። ይህ ማለት ግን የየካቲት ስድሳ ስድስት «አብዮት» መሬትን ላራሹ አድርጓል ማለት አይደለም። በኢትዮጵያ ስለነበረው የመሬት ስሪት በብዛት የምናውቀው ነገር ቢኖር ለፖለቲካ ፍጆታ ሲሉ የግራ ፖለቲከኞች አጣመው በፈጠሩት ፕሮፓጋንዳ እንጂ በእውቀት ላይ በተመረኮዘ ጥናት አይደለም። መሬት ላራሹ ከታወጀ በኋላ መሬት ላራሹ ሳይሆን የመንግስት ሆኗል። የልቁንም በመሬት ላራሹ አዋጅ የኢትዮጵያ ገበሬ ከመሬት ላራሹ በፊት የነበሩትን መብቶች አጥቷል። በመሬት ላራሹ አዋጅ መሬት ካድሬ እንዳሻው የሚያዝዝበት የባለጊዜዎቹ የወያኔና የደርግ ንብረት ሆኗል።

የ1923ቱ የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ የመጀመሪያው ህገ መንግስት ለገበሬው የሰጠውን መብት ያህል ከዚያ በኋላ የመጡት ወያኔና ደርግ የጻፏቸው «ህገ መንግስቶች» አልሰጡትም። ምናልባትም መሬት ላራሹ ሲባል የሰማ ሁሉ በዚህ ግራ ሊጋባ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ነገሩ እውነት ነው። «ያ» ትውልድ በዘመኑ ያጠፋቸውን ብዙ ነገሮች በእውቀትና በእውነት እንዳንመረምር ከራሱ ጋር እስከዛሬ ሳይታረቅ እንዳለ በመኖሩ የዛሬዎችን ትውልዶች ጭምሮ ጥሞና እየነሳ በጨለማ ውስጥ እያዳከረን ይገኛል። የሆነው ሆኖ የ«ያ» ትውልድ «የመሬት ላራሹ» አብዮት የገበሬውን መብት ቀነሰው እንጂ አልጨመረውም። ይህንን እውነት ለማሳየት የወያኔ ስርዓትና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት የጻፏቸውን ህገ መንግስቶችና በሁለቱም ዘመናት ህገ መንግስቶች ውስጥ ለገበሬው የተሰጠውን መብት በሚመለከት የተጻፉ አንቀጾችን ማስተያየት በቂ ነው።

የወያኔ «ሕገ መንግስት» የንብረት መብትን በሚደነግገው አንቀጽ 40 ቁጥር ሶስት ላይ እንደሰፈረው «የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው።» ይላል። በዚሁ አንቀጽ በተራ ቁጥር ስምንት ላይ ደግሞ «የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል መውሰድ ይችላል» ይለናል። የወያኔ ህገ መንግስት « የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ» የሚለን እንደፈለገ በመንጠቅ ከንብረትም፣ ከሀብትም ውጭ አድርጎ ያፈናቅላል እንዳይባልና «እንዳያማህ ጥራው» ዘዴው እንዳይቀርበት ነው።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የመጀመሪያው ህገ መንግስት ያየን እንደሆነ ደግሞ መሬት የገበሬው የግል ንብረት እንደሆነ ይደነግግና በአንቀጽ ሰባ ስድስት ላይ «መንግስት ለህዝብ ጥቅም የሚሆን እንደ ምሽግ፣ እንደ መንገድ፣ እንደ ገበያ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን፣ እንደ ተማሪ ቤት፣ እንደ ሆስፒታልና እንደ ከተማ፤ ይህንንም የመሰለ ሥራ ሁሉ በገበሬ ርስት ላይ ለመስራት የፈለገ እንደሆነ፤ የሚያስፈልግ መሆኑ ለምክር ቤቱ ከቀረበ በኋላ፤ በህግ እንደተወሰነ ለባለርስቱ [ለገበሬው] የሚገባው ዋጋ ተሰጥቶት ቢፈቅድ ሌላ መሰሉን ለውጥ እንዲቀበል ተደርጎ እንዲለቅ ይደረጋል እንጂ ፤ ይህንን ለመሰለ ለህዝብ ጥቅም ካልሆነ በስተቀር ለትራፊ ጥቅም [for profit] ተብሎ የገበሬ መሬት እንዳይወሰድበት በህግ ተወስኗል።» ይለናል።

ከዚህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመጀመሪያው ህገ መንግስት እንደምንረዳው ለህዝብ ጥቅም [Public use] ካልሆነ በስተቀር እንደ ወያኔ ዘመን ገበሬውን ለንግድ ስራ፣ ለግለሰብ ባለሀብትና ለማንኛውም ትርፍ ነክ የኢኮኖሚ ተግባሮች ሲባል ከመሬቱ በምንም መልኩ አይፈናቀልም። የወያኔ ህገ መንግስት ግን ገበሬው ለንግድ ስራ፣ ለግለሰብ ባለሀብትና ለማንኛውም ትርፍ ነክ የኢኮኖሚ ተግባሮች ሲባል በማንኛውም ጊዜ ከመሬቱ እንዲፈናቀል ይፈቅዳል። በወያኔ ህገ መንግስት በንጉሱ ዘመን የገበሬው የግል ንብረት የነበረው መሬት የካድሬ ሀብት ሆኗል። በተጨማሪም የወያኔ ህገ መንግስት በንጉሱ ዘመን ገበሬው የነበሩትን መሬት የመግዛትና የመሸጥ፤ አስይዞ የመበደር፤ የመለወጥና የመሳሰሉትን ያልተሸራረፉ መብቶች ቀንሷቸዋል። በወያኔ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ ገበሬ ገበሬ ከመሆን በስተቀር ሌላ አማራጭ የለውም። ከተማ መግባት፣ የስራ ዘርፍ መቀየር፣ እርሻውን ማስፋፋት፣ ወዘተ ቢፈልግ የመወረስ ጥላ ስለሚያንዣብብበት ማድረግ አይችልም።

ዛሬ ለኢትዮጵያ «ገበሬ» ልማትና የከተሞች መስፋፋት ወደ ሀብት የሚሸጋግሩት ጸጋዎች ሳይሆኑ መወረስንና መነጠቅን አፋጥነው ወደ ከፋ ድህነት የሚወስዱት ስጋቶቹ ናቸው። ዛሬ የምናያቸው በአዲስ አበባ ዙሪያና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች እየተካሄዱ ያሉት የገበሬ አመጾች የዚህ የመነጠቅ ሥጋት ውጤቶች ናቸው።

እንግዲህ! በመሬት ላራሹ የገበሬውን መብት ሊጨምር ይቅርና ቢያንስ በሶስት ነገር ቀንሷል፤

1. የመጀመሪያ በመሬት ላራሹ ገበሬው ለህዝብ ጥቅም ለሚውሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች ግንባታ ብቻ ሳይሆን ለንግድ ስራ፣ ለግለሰብ ባለሀብትና ለማንኛውም ትርፍ ነክ የኢኮኖሚ ተግባሮች ሲባል በማንኛውም ጊዜ ከመሬቱ ይፈናቀላል። ከመሬት ላራሹ በፊት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ግን ለህዝብ ጥቅም ለሚውሉ

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች ግንባታ ብቻ እንጂ ለንግድ ስራ፣ ለግለሰብ ባለሀብትና ለማንኛውም ትርፍ ነክ የኢኮኖሚ ተግባሮች ሲባል በማንኛውም ጊዜ ገበሬው ከመሬቱ እንዳይፈናቀል መብቱ በህገ መንግስት የተረጋገጠ ነበር።

2. ሁለተኛ በመሬት ላራሹ መሬት የገበሬው የግል ሀብት አይደለም። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ግን መሬት የገበሬው የግል ሀብት ነበር።
3. ሶስተኛ በመሬት ላራሹ ገበሬው መሬት የመግዛትም ሆነ የመሸጥ መብት የለውም። ከመሬት ላራሹ በፊት በንጉሰ ነገስቱ ዘመነ መንግስት ግን ገበሬው መሬት የመግዛትም ሆነ የመሸጥ ያልተገደበ መብት ነበረው። የገበሬውን መብት መጨመር የነበረበት መሬት ላራሹ፤ ለውጥ መጣ ተብሎ ገበሬው በአዋጁ የነበሩትን መብቶች እንዲያጣ ተደርጓል።

«ያ» ትውልድ ግን ዛሬም መሬት ላራሹን እንደ አኩሪ ድል የገበሬው መብት ጨምሯል እያለ በባዶው ያደናግራል። የ «ያ» ትውልድ የመሬት ላራሹ አብዮት መሬትን ከገበሬው ነጥቆ መሬትን ለካድሬ አደረገ። <u>የ «ያ» ትውልድ የመሬት ላራሹ አብዮት መሬትን የመንግስት ሀብት ስላደረገ የዛሬዋ ኢትዮጵያ ድሀ ለሀብታም ሲባል የሚፈናቀልባት አገር ሆናለች።</u> በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ገበሬ ብቻ ሳይሆን ጭሰኛና የመሬት ከበርቴዎችም ነበሩ። በዚህ ነባራዊ ሁኔታ ላይ መታወጅ የነበረበት የመሬት ላራሹ አዋጅ ገበሬውንም፣ ጭሰኛውም፣ የመሬት ከበርቴውንም ወደ ካድሬ ጭሰኛነት የሚያወርድ ሳይሆን ሁሉንም የመሬት ባለቤት የሚያደርግ አዋጅ ነበር። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የነበረ ጭሰኛ የመሬት ባለቤት የመሆን እድሉ ሰፊ ነበር። በጉልበቱ ሰርቶ በሚያገኘው ጥሪት መሬት ገዝቶ የመሬት ባለቤት መሆን ይችል ነበር። በዚያ ዘመን መሬት የጠበበው ገበሬው ከራሱ የእርሻ መሬት በተጨማሪ በጭሻኝነት ተከራይቶ ገቢውን ከፍ ለማድረግ ይተጋ ስለነበረ ጭምር ነው። በወያኔ ዘመነ መንግስት ግን የካድሬ ጭሰኛ የሆነው ባተሌ አርሷደር ባለመሬት የመሆን እድሉ ዝግ ወይንም 0% ነው። በመለስ ዜናዊ ቋንቋ በወያኔ ዘመነ መንግስት የካድሬ ጭሰኛ የሆነው ያገራችን ባተሌ አርሷደር ወደ መሬት ባለቤትነት ደረጃ የሚያድገው በወያኔ መቃብር ላይ ነው።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የነበረው ጭሰኛ መሬት ተከራይ ግንኙነቱ ከአንድ የመሬት ባለቤት ጋር ብቻ ነበር። የንጉሱ መንግስት ለጭሰኛው እሩቅ ነበር። በመሬት ላራሹ ግን የወያኔ ጭሰኛ የሆነው ባተሌ አርሷደር ቀበሌ፣ የገበሬ ማህበር፣ ወረዳ፣ ክልል፣ ፓርቲ.. .. የሚባሉ ተቋማትንና ቁጥሩ የማያልቅ የካድሬ መንጋ አለቃ አለበት። ይሄ ሁሉ አለቃ በወያኔ ዘመኑ ጭሰኛ ላይ አዛዥና ናዛዥ ነው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት እንደ ደብረ ዘይት የግብርና ምርምር ጣቢያ፣

አለምማያ የግብርና ኮሌጅ፣ አምቦ እርሻ ኮሌጅ፣ የጭላሎ ግብርና ልማት ድርጅት፣ የወላይታ ግብርና ልማት ድርጅት፣ የአርሲ የገጠር ልማት ድርጅት፣ ወዘተ. . አይነት ገበሬውን በእውቀት የሚመክሩ ተቋማት ነበሩ። በወያኔ ዘመን ግን ጭሰኛው አርሷደር ምንም ውጤት በማይሰጡ የፕሮፓጋንዳ ስብሰባዎች ታጉሮ ፍሬ ቢስ የካድሬ ዲስኩሮችን ጸሀይ እያንቃቃው ሲያዳምጥ ይውላል። መሬት ላራሹ ታውጆ የተገኘው ውጤት ቢኖር ራሱን መመገብ የማይችል አራሽ ነው። ሆኖም ግን አዋጁ ከመፍትሔነት ይልቅ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት ቀድሞ የታያቸው በርካታ ባለሞያዎች ስጋታቸውን ገልጸው ነበር። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ የእርሻ ሚኒስቴር የነበሩት የሀገሪቱ ቁንጮ የሰብል ተመራማሪ፣ መምህርና አስተዳዳሪ ዶክተር ዳኛቸው ይርጉ ደርግ የካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም. ያወጀው የመሬት ላራሹ አዋጅ የሚያስከትለውን የርሀብ መዘዝ አበክረው ከተናገሩት ኢትዮጵያውያን ልሂቃን መካከል ቀዳሚው ነበሩ። ዶክተር ዳኛቸው ይርጉ በዚህ ጥረታቸው ያተረፉት ነገር ቢኖር ደብዛቸው መጥፋት ነበር።[9]

ዶክተር ዳኛቸው በተናገሩት ትንቢት መሰረት ረሀብትና የምግብ እጥረት አብረውን የሚኖሩ እውነታቸው ከሆኑ ዘመናት ተቆጠሩ። ኢትዮጵያም ላለፉት አርባ ሁለት አመታት ራሱን የቻለ የርሀብና የልመና ኢኮኖሚ ፈጥራ በታሪኳ አድርጋው የማታውቀውን ስንዴና ዘይት አስመጭ አገር ሆናለች። በዚህም ብቸኛ ተጠቃሚዎች የስርዓቱ ታማኞች ናቸው።

የብዙ ሳይንሳዊ ምርምር ግኝቶች ባለቤት የሆነው የሀገራችን ታላላቅ የእርሻ ምርምር ጣቢያዎችን አቋቁመው የመሩት ዶክተር ዳኛቸው ይርጉ በጠመኛ ፊት የሚያምኑበትን እውነት ተጋፍጠው በወታደሮች [በደርጎች] እና ቀደም ብሎ በዳይሬክተርነት ይመሩት በነበረው የጭላሎ ግብርና ልማት ድርጅት ውስጥ ሰርገው በገቡ ኢህአፓዎችና የመሬት ይዞታ ሚንስትርን በተቆጣጥሩ መኢሶኖችና አነጎች መሀል እውነቱን ተናግረው ለሞያቸውና ለኢትዮጵያ ህዝብ ያላቸውን ታማኝነት በመጠበቅ ወለጋ ለስራ በሄዱበት በህይዎታቸው ዋጋ ከፍለዋል።

የካቲት 1967 ዓ.ም. የታወጀውና በተለምዶ «የደርግ የመሬት ላራሹ አዋጅ» እየተባለ የሚታወቀው የገጠር መሬት አዋጅ የኦነግ፣ የኢህአፓና የመኢሶን ፕሮጀክት ነው። የመሬት ላራሹ አዋጅ ሲረቀቅ ተሳታፊ የነበረው የመኢሶኑ አንዳርጋቸው አሰግድ በመጋቢት 1992 ዓ.ም. «በአጭር የተቀጨ ረጅም ጉዞ፡- መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ» በሚል ርእስ አተዘጋጅቶ ባሳተመው

[9] *አበበ ይርጉ፤ ለእውነት የተሰዋው ሰማዕት፤ የሊቁ የዶክተር ዳኛቸው የሕይወት ታሪክ ስለአጠፋፉ የተደረገ ክትትል፤ 2004 ዓ.ም. ገጽ107–177.*

መጽሐፍ ውስጥ እንደነገረን የመሬት ላራሹ አዋጅ ሲዘጋጅ የመሬት ይዞታ ሚንስትሩ ዘገየ አስፋው፣ ባሮ ቱምሳ፣ ዲማ ነገዎና ፍቃዱ ዋቅጅራ ግንባር ቀደም ተሳታፊዎች ነበሩ።[10] እነዚህ አራት ግንባር ቀደም የመሬት ላራሹ አዋጅ አዘጋጆች የኦነግ መስራች ፋኖዎች ናቸው። ዲማ ነገዎ የኦነግ መስራችና የመጀመሪያው ሊቀመንበር መሆናቸውን ሁላችሁ የምታውቁ ይመስለኛል። እነዚህ የኦነግ ፋኖዎች፤

1. የገጠር መሬት የተባለ ሁሉ የመንግስት ይዞታ እንዲሆን፤
2. ማንኛውም ተቋምም ሆነ ግለሰብ መሬትን በግል ንብረትነት ለመያዝ የማይችል መሆኑን፤
3. ማንም ሰው መሬቱን የመሸጥ፣ የመለወጥና የማውረስም ሆነ በወለድ እግድ ለማስያዝ የማይችል መሆኑን በመሬት ላራሹ አዋጅ አስደነገጉ።

ይታያችሁ! ከመሬት ላራሹ በፊት፤ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የራሱ የመሬት ባለቤት የነበረውን የኦሮሞ ገበሬ [ ጭሰኛ አላልሁም] የመሬት ባለቤትነት መብት የነጠቀው ለኦሮሞ እቆረቆራለሁ የሚለን ኦነግ ነው። ኦነጋውያን ባዘጋጁት የደርግ የመሬት ላራሹ አዋጅ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የመሬት ባለቤት የነበረው የኦሮሞ ገበሬ መሬቱ ተነጥቆ የደርግ ጭሰኛ ሆነ። በሌላ አነጋገር የኦሮሞ ገበሬ በደርግ ዘመንና ለወያኔ ዘመን የመሬት ገፈፋ ያመቻቸ ኦነግ ያዘጋጀው የመሬት ላራሹ አዋጅ ነው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ህገ መንግስት የግል የመሬት ባለቤትነት ማዕረግ የተጎናጸፈው የኦሮሞ ገበሬ በኦነግ የመሬት ላራሹ አዋጅ መብቱ ተገፎ የደርግና የወያኔ ጭሰኛ ሆነ። ዶሴው ሲወጣ ቁልጭ ብሎ የሚታየው እውነት ይህ ነው። የኦሮሞን ገበሬ የመሬት ባለቤትነት መብት የገፈፈው ኦነግ ዛሬ ላይ ስለኦሮሞ ገበሬ የመሬት ባለቤት አለመሆን ሲናገር ስሰማ ግርም ይለኛል።

## 2.3 ኦሮምኛን ለማጥፋት ሙከራ ነበረ ወይ?

ሌላው የግራ ፖለቲካ እውቀት ያሳከለው «የድሮ ስርዓት» የሚባለው የንጉሰ ነገስቶቹ ዘመን ኦሮምኛንና ኦሮሞን አጥፊ እንደነበር እየተደጋገመ የሚነገረው ፕሮፓጋንዳ ነው። የአጥፊው «ስርዓት» መናኸሪያ ነበር ከሚባለው ከአራት ኪሎው ቤተ መንግስት አንድ ኪሎ ሜትር በወፍ በረር ብትሄዱ የኦሮሞ ገበሬ ኦሮምኛውን እያወራ ሲያርስ ታገኙታላችሁ። «አጥፊ» የተባለው ስርዓት አራት ኪሎ ተቀምጦ ከአንድ ኪሎሜትር ወፍ በረር ርቀት ላይ እንዴት ኦሮምኛ የሚናገር ገበሬ ተገኘ? ብላችሁ ብትጠይቁ መልስ አታገኙም። ይህ ከቤተ መንግስቱ አንድ ኪሎ ሜትር የወፍ በረር ርቀት ላይ የሚኖረው የኦሮሞ ገበሬ ያመረተውን የሚሸጠው ቤተ መንግስቱ አቅራቢያ በሚገኘው አቧሬ ገበያ

---

10 *ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፣ እኛና አብዮቱ፡ ገ.181-182*

ነበር። በርግጥ አራት ኪሎ የነበረው መንግስት ኦሮሞና ኦሮምኛን አጥፊ ቢሆን ኖሮ ከቤተ መንግስቱ በአንድ ኪሎ ሜትር የወፍ በረር ርቀት ላይ የኦሮሞ ገበሬ ጥርት ያለ ኦሮምኛ ሲያወራ አይገኝም ነበር። በርግጥ ኦሮሞና ኦሮምኛ ከአጼ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ለመቶ አመታት ያህል እንዲጠፋ ከተዘመተበት ለምን ኦሮሞና ኦሮምኛ ከስርዓቱ ማዕከል ከአራት ኪሎ ቤተ መንግስት በአንድ አንድ ኪሎ ሜትር የወፍ በረር ርቀት ላይ ኦሮሞ አልጠፋም? መቶ አመት በመንግስት ደረጃ እንዲጠፋ የተዘመተበት ቋንቋ እንዴት ሌላው ቢቀር ከአራት ኪሎ አፍንጫ ሳይጠፋ ቀረ? የሚሉ ጥያቄዎች ቢነሱ መልስ የላቸውም።

ሌላው ገራሚው ነገር «ኦሮምኛ ለማጥፋት ተንቀሳቅሶ ነበር» የተባለው ስርዓት ቁንጮ የነበሩት ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኦፊሴል ደረጃ የታወጀ አይሁን እንጂ በየሄዱበትና በቤተ መንግስታቸው ውስጥ ሳይቀር ኦሮምኛን ማውራታቸው ነው። ኦሮሞንና ኦሮምኛን ለማጥፋት የተንቀሳቀሱ ንጉሰ ነገስት actively ለማጥፋት የተቀሳቀሱበትን ቋንቋ ሊናገሩ አይችልም።

በዚያ ዘመን ኦሮምኛ እንዲጠፋ ቢፈለግ ኖሮ በግዕዝ ፊደል የተጻፈው ኦሮምኛው መጽሀፍ መጽሀፈ ቁልቁሎ እንደ አቤ ጉበኛው አልወለድም መጽሀፍ ተሰብስቦ ዶግ አመድ ይሆንና የመስዕዋትነትን ጽዋ ይቀበል ነበር። ያ መንግስት actively ኦሮምኛ እንዲጠፋ የሰራ ቢሆን ኖሮ መጽሐፌ ቁልቁሎን ያሳተሙ ሰዎች እናሳትም ሲሉ አታሳትሙም ተብለው ይከለከሉ ነበር።

በዚያ ዘመን ኦሮምኛ ለምን የትምህርት ቋንቋ አልሆነም? የሚል ጥያቄ ሲነሳ እሰማለሁ። ለዚህ ጥያቄ እስካሁን ድረስ ሲሰጥ የነበረው መልስ የራሳቸውን መንግስት ለመመስረት በታገሉ የግራ ፖለቲከኞች አውድ ነው። በትምህርት ሒደት ውስጥ ያለፍንና ስለ ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት የምናውቅ ሰዎች እንደምንገነዘበው በዚያ ዘመን ኦሮምኛ የትምህርት ቋንቋ ያልሆነው በግራ ፖለቲከኞች እንደተስተጋባው ቋንቋውን ለማጥፋት ታስቦ ሳይሆን በኦሮምኛ ትምህርት ለመጀመር አንደኛ ኦሮምኛ የጽሁፍ ፊደል ስላልነበረውና የጽሁፍ ፊደል የሌለው ቋንቋ የትምህርት ቋንቋ የሆነበት ሁኔታ በአለም ላይ ስለሌላ፤ ሁለተኛ በቋንቋው የሰለጠነ አስተማሪ ባለመኖሩ፤ ሶስተኛ በኦሮምኛ ቋንቋ የተዘጋጁ የማስተማሪያ መጽሀፍ፣ የማጣቀሻ መጽሔቶችና የንባብ መሳሪያዎች ባለመኖራቸው የተነሳ ኦሮምኛ የትምህርት ቋንቋ ሊሆን አልቻለም። እንኳን በዚያ ዘመን ዛሬ በምንኖርበት የሰለጠነ ዘመን እንኳ ከኢትዮጵያ 85 ቋንቋዎች መካከል የአንደኛ ደረጃ ማለትም ከ፲ኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ የትምህርት ቋንቋ የሆኑት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቁጥር ከ25 በታች

ነው።[11] የኢትዮጵያን የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ማለትም ከ7ኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ትምህርት የሚሰጥባቸውን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቁጥር ካየን ደግሞ ትምህርት የሚሰጠው ደግሞ በአምስት ቋንቋዎች ብቻ ነው[12]። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቋንቋ የሆነ አንድም የኢትዮጵያ ቋንቋ የለም።

እንግዲህ ከ85 የአገራችን ቋንቋዎች ውስጥ የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት በ25 ቋንቋዎች የሚሰጠው፤ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች ብቻ ትምህርት የሚሰጠው፤ በአንድም የአገራችን ቋንቋ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የማይሰጠው አንድም ቋንቋዎቻችን ፊደል ስለሌላቸው፤ ሁለትም በቋንቋዎቹ የሰለጠነ የሰው ሀይል ስለሌለና ሶስትም በቋንቋዎቹ የተዘጋጀ የማስተማሪያ መጽሀፍ፣ የማጣቀሻ መጽሔቶችና የንባብ መሳሪያዎች ስለሌሉ ነው። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ «በነገስታቱ ዘመን ኦሮምኛ የትምህርት ቋንቋ ያልሆነው ኦሮምኛ እንዲጠፋ ስለተፈለገ ነው» የሚለው ፕሮፓጋንዳ ፍፁም መሰረተ ቢስና አላዋቂነት የተሞላበት ልክና ለከት የሌለው ጥላቻ ውጤት ነው።

ከምንም በላይ የሚገርመው በዚያ ዘመን ከኦሮሞዎች አልፎ ኦሮሞ በብዛት በሚኖርባቸው የአገራችን ክፍሎች ይኖሩ የነበሩ ሚሊዮን አማሮችና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ሳይቀር ይናገሩት የነበረውን ኦሮምኛ ቋንቋን እንዲጠፋና እንዳይስፋፋ ተደርጎ ነበር የሚለው ክስ terminal ዲግሪ በደረሱ ሰዎች ጭምር ዛሬም ድረስ እየቀረበ መሆኑ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ የያ ትውልድ ፖለቲከኞችና ወራሾቻቸው በዲግሪ ማማ [terminal degree] ሲደርሱ ለሀላፊነት ያንሳሉ፤ እየተማሩ ሲሄዱ የሚስቱት እጥፍ ድርብ [exponentially] ይጨምራል። በእውነቱ አነገ እንደሚለው ኦሮምኛ ባለፈ መቶ አመት እንዲጠፋ actively የተዘመተበት ቢሆን ኖሮ አይደለምና ከኦሮሞ ውጭ ቋንቋውን የሚናገሩ ሌሎች ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ሊኖሩ ቀርቶ እንደ ጋፋት ስለመኖሩ የሚናገር ምልክት እንዳይኖር ተደርጎ ይጠፋ ነበር።

---

11 *Seidel, K. (2009). Changes in Ethiopia's Language and Education Policy –Pioneering Reforms? Proceedings Paper: 16th International Conference of Ethiopian Studies, Trondheim 2-7 July 2007.*

12 *Vujcich, D. (2013). Policy and Practice on Language of Instruction in Ethiopian Schools: Findings from the Young Lives School Survey.*

## 2.4 ተራማጁ ማነው? ኋላ ቀሩስ? [በተለይ በችግር አፈታት ዙሪያ]

«ኋላቀር» ተብሎ ላለፉት አርባ ሁለት አመታት የተዘመተበት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት አንጻራዊ ተራማጅነት በኋላ ከመጡት ሁለት ኮምኒስት ስርዓቶች ጋር ሊወዳደር የሚችል አይደለም። መለስ ዜናዊ የሚባለው የትግራይ ሽፍቶች አለቃ አንድ ጊዜ ቶጎ ሎሜ ላይ ንጉሰ ነገስቱ በመሰረቱት የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ባደረገው ንግግር የነክዋሜ ኑክሩማህና የነጆሞ ኬንያታ ልጆች ይታዘቡኛል ሳይል ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን «አድሀሪ» ወይንም Reactionary ሲል ተሳልቋል። በእውነቱ በተራማጅነት መስፈርት መንግስቱ ኃይለ ማርያምም ሆነ መለስ ዜናዊ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ሊወዳደሩ አይችሉም። መንግስቱን ለጊዜው ልተወውና ንጉሰ ነገስቱን «አድኃሪ» ሲል የተሳለቀውን መለስ ዜናዊን ግን «አድሀሪ» ካላቸው ንጉሰ ነገርስት ጋር በመስፈርት ማወዳደር እፈልጋለሁ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሰ ነገስትነት ሥልጣን ከመረከባቸው በፊት ማንም ሳይጠይቃቸው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መመዘኛ ዘመናዊ ከሚባለው በጃፓን ሥራ ላይ ከነበረው «የማጅ ዘውዳዊ ህገ መንግስት» ጋር የሚወዳደር ዘውዳዊ ህገ መንግስት በስራ ላይ እንዲውል አድርገው ነበር። ኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊ አስተዳደር የምታደርገውን ሽግግር በአንድ ደረጃ ከፍ ያደረገ መሪ ኋላቀር የሚሆነው በደንቆሮው መለስ ዜናዊ መመዘኛ ብቻ ነው። ከፍ ብዬ የጠቀስሁላችሁ የመሬት ባለቤትነት መብት አንቀጽ የዚህ ህገ መንግስት አካል ነው። የአምባሳደር ዘውዴ ረታን «የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት» መጽሀፍ ያነበባችሁ ሁሉ ህገ መንግስቱ በሚረቀቅበት ወቅት ተራማጆቹ ፊታውራሪ ተክለሀዋሪያት ተክለ ማሪያምንና ብላቴና ጌታ ህሩይ ወልደስላሴ ከወግ አጥባቂ መሳፍንቶች የገጠማቸውን ተቃውሞ ንጉሰ ነገቱ ከተራማጆች ጋር ወግነው ኢትዮጵያን እንዴት አድርገው ከተለመደው የመሳፍንቶች ተጽዕኖ አውጥተው በህግ የምትገዛ አገር ለማድረግ እንደጣሩና የወግ አጥባቂ መሳፍንቶችን ግፊት በስልትና በጥበብ በማለፍ ህገ መንግስት እንዳቆሙ ታስታውሳላችሁ።[13] የዚህ ህገ መንግስት አላማ በየ አካባቢው ህዝቡን እንደግል ንብረታቸው ይቆጥሩት የነበሩትን መሳፍንቶች ስልጣን የመገደብና ህጉ ከመውጣቱ በፊት በአገሪቱ ውስጥ ደም ያፋሰሱ አንገብጋቢ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችንም ህጋዊ ስርዓት ለማስያዝ ነበር። ይህ ህገ መንግስት በተለያየ ጊዜ የተነሱ የህዝብ ትያቄዎችን ተከትሎ ሁለት ጊዜ ተሻሽሏል።

---

[13] *ዘውዴ ረታ፡ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት[1923–1948], Laxmi Publications, 2004 ዓ.ም. ከገጽ 25–58.*

«ተራማጅ ነኝ» የሚለው የመለስ ዜናዊ ህገ መንግስት ከነ ስህተቱ ሳይሻሻል ሀያ አራት አመታት ሆኖታል። የመለስ ዜናዊ ህገ መንግስት የማሻሻያ አንቀጾች ቢኖሩትም ማሻሻያ የጠየቁ በርካቶች ግን «ህገ መንግስቱን ለመናድ በሚል» ለእስር፣ እንግልትና ሞት ተዳርገዋል። ብዙ ሰው እንደሚያስታውሰው ባለፈው አመት የመለስ ዜናዊን ህገ መንግስት እንዲሻሻል ጥያቄ ያቀረቡት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞቹ እነ ዳኛ ግዛቸው ምትኩ በወያኔው አሻንጉሊት የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ፊት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛነት ሹመታቸው ተገፎ ከዳኝነት ስራቸው ተሰናብተዋል።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ1966 ዓ.ም. ህዝቡ ሰልፍ መውጣት ሲጀምር፤ ተማሪዎችና የኢትዮጵያ ወታደሮች ጥያቄዎችን ሲያቀርቡ ከሳቸው በኋላ የመጡት ሁለቱ አገዛዞች ያላደረጓቸውን ሶስት አበይት ታሪካዊ ተግባሮች በማከናወን በመንግስታዊ መዋቅራቸው ውስጥ ተቋማት ፈጥረው በስርዓታቸው [with in the system] ውስጥ ህዝባዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ተንቀሳቅሰዋል፤

1. በወቅቱ ተከስቶ ለነበረው ርሀብ ተቋማዊ ምላሽ ለመስጠት በ1966 ዓ.ም. በአዋጅ በፓርላማ ጸድቆ የተመሰረተ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የሚባል ተቋም በመስሪያ ቤት ደረጃ አቋቋሙ። ቀደም ሲል በአቶ ሽመልስ አዱኛ[14] በኋላ ደግሞ በሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ይመራ የነበረው ይህ መስሪያ ቤት የሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ህይወት በማትረፍ ረገድ የተጫመተውን ታሪካዊ ሚና የሻለቃ ዳዊትን «የደም እንባ» መጽሀፍ ያነበባችሁ ታስታውሱታላችሁ።[15]

2. ሁለተኛው የንጉሰ ነገስቱ ታሪካዊ ስራ ስልጣናቸውን ያለ አግባብ ተጠቅመዋል የተባሉ የንጉሰ ነገስቱ ባለስልጣናት እንዲመረመሩ በ1966 ዓ.ም. አሁንም በንጉሰ ነገስቱ ፓርላማ ጸድቆ የተመሰረተው መርማሪ ኮሚሽን ወይንም Inquiry comission ነው።[16] ይህ ተቋም ስራውን ሳይጨርስ መንግስቱ ኃይለ ማርያም ስራውን አስቁሞ እንዲመረመሩ የታሰሩ

---

[14] *"Africa: Strategy to Improve Food Security Plans in the Continent". allAfrica.com. 9 April 2008. Retrieved 2016-8-22.*

[15] *Dawit Wolde Giorgis (1989) Red Tears: War, Famine and Revolution in Ethiopia. Red Sea Press, Trenton, N.J, PP. 22-32*

[16] *Mesfin, Weldemariam. Interview by Sisay Agena. Yesamentu Engeda. ESAT. Washington DC: Dec 6, 2015. Televivion.*

የሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣናትን በግፍ በመግደል ኢትዮጵያን ራቁሯን እንዳስቀራት ለናንተ መንገር ለቀባሪው ማርዳት ነው።

3. ሶስተኛው የንጉሰ ነገስቱ ታሪካዊ ተግባር ራሳቸውን ንጉሰ ነገስቱን «ስልጣናቸው ይገደብ» ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት [አሁንም በንጉሰ ነገስቱ ፓርላማ የጸደቀ ነው] ያቋቋሙት የህገ መንግስት አርቃቂ ኮምሽን ነው። ይህ ኮሚሽን በ1966 ነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ስራውን ቢጨርስም ደርግ ረቂቅ ህገ መንግስቱን አግዶ መስከረም 2 ቀን 1967 የሞት አዋጅ ስላወጣ ኢትዮጵያ ያሏት ሊቃውንቶች ተሰባስበው ጭንቅላታቸውን በመጭመቅ ያረቀቁት ህገ መንግስት በሻለቃ መንግስት ኃይለ ማርያም ያስቾኳይ ጊዜ አዋጅ ተተካ።[17]

እንግዲህ! ያኔ የሕዝብ ጥያቄ እንደዛሬው «አሸባሪዎችና ጸረ ሰላም ኃይሎች የፈጠሩት ነው» ሳይባል በመንግስታዊ መዋቅሩ ተቋማዊ በሆነ መልኩ መልስ በመስጠት ረገድ ያን ያህል ተራማጆች ነበርን።

መለስ ዜናዊና የገነባው ስርዓት ግን ህዝቡ ሲጠይቅ፤ ተማሪዎችና የኢትዮጵያ ገበሬዎች ሰልፍ ሲወጡ የሰጠውን ምላሽ ነጋሪ የምትፈልጉ አይመስለኝም። የመለስ ዜናዊ ስርዓት ህዝቡ ለጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ ለስድስት ወር የሚቆይ «የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ» የሚባል የግድያ አዋጅ ነው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ህዝቡ ሰልፍ ወጥቶ ያን ያህል ህዝባዊ ንቅናቄ ሲፈጠር በጥይት የተገደለው አንድ ሰው ብቻ ነበር።[18] በወያኔ ዘመን ግን ባለፈው አንድ አመት ውስጥ ብቻ በግፍ የተገደሉት ኢትዮጵያውያን ቁጥር በሺዎች እየተቆጠረ ነው። «የትግራይ የበላይነት ይቁም» በሚል ህዝቡ በሰልፍ ወጥቶ ለጠየቀው ህዝባዊ ጥያቄ ወያኔዎች የሰጡት መልስ ከትግራይ ውጭ ባሉት የአገሪቱ አካባቢዎች ለስድስት ወር የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና የትግራይን የበላይነት ሸቅብ ገንብቶ የተቀረውን የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ የበለጠ ቁልቁል የሚደፋ ምላሽ ነው።

ከወርቅ ህዝብ ተፈጠርሁ ይለን የነበረው መለስ ዜናዊ ተሰርቶ ያላለቀ ግለሰብ ነበር። ዛሬ አንድ ቅንጫቢ ነገር ካነበበና ስለአንድ ነገር ቁንጽል ወሬ ከፈረንጅ አፍ ከሰማ፤ ሌሊቱን ስለዚያ ስላነበበው ቅንጫቢ ነገር ወይንም ከፈረንጅ አፍ ስለሰማው ቁንጽል ወሬ በጉዞ ማስታወሻ ደብተሩ ሲሞነጭር

---

17 *ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ የሕይወቴ ታሪክ፤ ገጽ 160- 147*

18 *ነገደ ጎበዜ፤ ይድረስ ለግንቦት ከየካቲት፤ ገጽ 169.*

ያድርና በበነጋታው ወደ አገራዊ «ፖሊሲ» ይቀይረው ነበር። ADLI፤ ውሀ ማቆር፤ BPR፤BSC፤ ማይክሮ ፋይናንስ፤ ውጤት ተኮር፤ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፤ ልማታዊ መንግስት፤ ወዘተ የሚባሉት የወያኔ «ልማታዊ መስመሮች» ሁሉ በዚህ መልኩ «አገራዊ ፖሊሲ» የሆኑ ናቸው። ከዚያም በዚህ መልክ «አገራዊ ፖሊሲ» ባደረጋቸው ፖሊሲዎች ላይ የፈረመው ቀለም ሳይደርቅ ዛሬ ላይ ባነበበው ሌላ ቁንጽል ነገር ወይንም ከፈረንጅ አፍ በሰማው ቅንጫቢ ወሬ ይለውጠዋል። ባጭሩ መለስ ዜናዊ የአገር ፖሊሲን ያህል ትልቅ ነገር እንደ መስሪያ ቤት ማኑዋል በየቀኑ እየቀያየረ ሲያወናብድ የኖረና ተሰርቶ ያላለቀ ሰው ነበር።

## 2.5 እውን የድሮ ስርዓት እየተባለ የሚነቀፈው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ብዝሀነትን አላስተናገደም?

ቀደም ብዬ በኢትዮጵያ ረጅም የታሪክ ዘመን ውስጥ በየጊዜው ስልጣን በያዘው የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግስታት ውስጥ በአስተዳደር ሥልጣንና በሥራ ድርሻውም ክፍፍል ላይ እንደወቅቱ ሁኔታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሔረሰብ፣ ነገድና ጎሳ የተካፈሉበት ለመሆኑ ማስረጃ የሚያሻው አለመሆኑን ገልጫለሁ። ከዚህ እውነት አንጻር የተፈጠሩት ፋሽስት ወያኔዎችና አነጎች ግን በተለያየ ጊዜ በሚሰሩት ዶክመንተሪና በፕሮፓጋንዳ ዲስኩራቸው «ብዝሀነትን» ወይንም diversityን ከደደቢት በረሀና ከሞቃድሾ የዚያድ ባሬ ቤተ መንግስት ዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግስት ስበው ያመጣጡት አንዳች አዲስ ጽንሰ ሀሳብ አድርገው እየተሰበኩ ይገኛል።

ላስተዋለው ግን በተለይ በኢትዮጵያ ንጉሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ብዝሀነት አዲስ አይደለም፤ በቤተ መንግስት ደግሞ በጉልህ ይታይ ነበር። አዎ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በቤተ መንግስታቸው ከነ ራስ አበበ አረጋይ፤ ከነ ራስ ስዩም መንገሻ፤ ከደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፣ ከመንገሻ ስዩም፤ ከሱልጣን አሊ ሚራህ፣ ከነ ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ፤ ከነ ራስ መስፍን ስለሺ፣ ከነ ጀኔራል ጃጋማ ኬሎ፣ ከነ ተድላ ባይሩ፣ ከነ ሐረጎት አባይ፣ ከነ አስፍሀ መልደ ሚካሄል፣ ከነ ይልማ ደሬሳ፣ ከነ ፊታውራሪ መኮነን ዶሪ፣ ከነ ታደሰ ብሩ፣ ወዘተ ጋር ሲገናኙ በአማርኛ ያወሩ ነበር። እንኳን ያንድ አገር ሰዎች የተለያዩ አለም መሪዎች እንኳ ዋይት ሀውስ ሲሄዱ ከአሜሪካን ፕሬዝደንቶች ጋር የሚነጋገሩት በእንግሊዝኛ ነው። ሁለት ሰዎች ይግባቡ ዘንድ በአንድ ቋንቋ ማውራታቸው ግድ ነው። «የብዝሀነት አባት» ተደርጎ በካድሬዎቹ የሚሰበክለት መለስ ዜናዊም ከነጀኔራል አባዱላ ገመዳ፣ ከነ አባተ ኪሾ፣ ከነ ኩማ

ደመቅሳ፣ ከነ አብዱል መድጅ ሑሴን፣ ከነ ግርማ ብሩ፣ ከነ ጁኔይድ ሳዶ፣ ከነ አልማዝ መኩ፣ ከነ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጋር በዳግማዊ ምኒልክ ቤተ መንግስት ሲገኛኝ የሚያወራው በአማርኛ ነበር።

ሌንጮ ለታም በመስ ዜናዊ ቦታ ቢቀመጥ ኖሮ ከነ ስዬ አብርሀ፣ ከነ ካሱ ኢላላ፣ ከነ አብዱል መጂድ ሑሴን፣ ከነ መብርሀቱ ገብረሕይወት፣ ከነ ክንፈ አብርሀ ጋር ሲገናኝ የሚያወራው በአማርኛ ነበር። ልዩነቱ ወንበሩ ላይ የሚቀመጡት ሰዎች እንጂ የብዝሀነት ጉዳይ አይደለም። ሆኖም ግን ታሪክ የሚጻፈው በየዘመኑ አሸናፊዎች ነውና የኢትዮጵያ ብዝሃነት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቤተ መንግስት ያልነበረ፤ በመለስ ዜናዊ ቤተ መንግስት ግን ከደደቢት ተስቦ እንዳዲስ የተጀመረ ተደርጎ አዲስ ተጻፈ። ዛሬ በአፍ የሚሰበከው «ብዝሀነት» የነጻነት ፍቺ ቢሆን ኖሮ «ብዝሃነት ተከበረ» በተባለበት በመለስ ዜናዊ ዘመነ መንግስት የኦሮምያ ምስለኔ ከነበረው ከኦሮሞው አባዱላ ገመዳ በላይ በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት የሸዋ ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት ኦሮሞው ራስ መስፍን ስለሺ የተሻለ ነጻነት አይኖራቸውም ነበር።

ሆኖም ግን የራሳቸውን አገር ለመመስረት የሚታገሉት የዘር ድርጅቶቹ አነግና ወያኔ ከፍ ሲል በንጉሰ ነገስቱ ዘመን የነበሩትንና በአንድነቱ ጊዜ የነበሩና እስከመጨረሻው ድረስ በኢትዮጵያዊነት አቋማቸው ጸንተው የቆሙትን የብሔረሰባቸው አባላት ስለኢትዮጵያ ያደረጉትን ሁሉ የከሀዲዎች ድርጊት አድርገው ሲያጣጥሏቸው ይውላሉ። በኢትዮጵያ አስተዳደር ውስጥ የብህዘነት ምልክቶች የነበሩት እነ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩም፣ ጄኔራል ጃጋማ ኬሎና አስፍሀ ወልደ ሚካዔል የዚህ የዘረኞች የከሀዲነት ክስ ሰለባዎች ናቸው። እነ ጀኔራል ጃጋማ ኬሎ ላገራቸው የሚገባቸው በማድረጋቸው በኦነጋውያን ዘንድ «ጎበናዎች» እየተባሉ እንዲሸማቀቁ ተደርገዋል። በቤተ ኦነግ «ጎበና» የሚለው ስም ሲጠራ የክህደት፣ የጸረ ኦሮሞነትና የጥፋት ተላላኪነት መገለጫ ሆኗል። በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ አዎንታዊ ሚና የተጫዎቱትና የየነገዳቸውን በጎነት ኢትዮጵያን ለመገንባት ያዋሉት ኦሮሞዎች፣ ጉራጌዎች፣ ወላይታዎች፣ ጋሞዎች፣ አደሬዎች፣ ሶማሌዎች ወዘተ ነበሩ። ከእነዚህ ነገዶች የተውጣጡ ፖለቲከኞችና አዋቂዎች ባለፈው መቶ አመት የኢትዮጵያ ዘመናዊ የመንግስት ታሪክ ውስጥ አዎንታዊ አሻራቸውን ያሳረፉ የብዝሀነት ማህተሞች ናቸው[19]።

---

19 *Christopher Clapham, Haile Selassie's Government (New York: Frederick A. Praeger Publishers, 1969.*

## 2.6 የአርበኛ ጠላት ማነው?

*የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የምህረት አዋጅ ሁላችሁም የምታውቁ ይመስለኛል።[20] ይህ የምህረት አዋጅ የታወጀው የአምስቱ የመከራ አመት አልቆ ነጻነታችን ሊመለስ ጥቂት ወራት ሲቀሩት ንጉሰ ነገስቱ በሱዳን በኩል አድርገው ጎጃም እንደገቡ በ1933 ዓ.ም. ነው። በአምስቱ የጥሊያን የወረራ አመታት ጀግኖች አባቶቻችን የተዋጉት ከሮም ከመጡ የፋሽስት ወታደሮች ጋር ብቻ ሳይሆን ለጥሊያን ካደሩ ባንዳ ኢትዮጵያውያን ጭምር ነበር። ጥሊያን ከኢትዮጵያ ስትባረር እስካፍንጫቸው ታጥቀው የነበሩት ባንዶችና ሲያደሟቸው በነበሩት አርበኞች መካከል የነበረው በጠላትነት የመተያየት ግንኙነት በምህርት አዋጁ ባይረግብ ኖሮ የብዙ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች ደም ይፈስ ነበር። ያ የምህረት አዋጅ ርስበርስ እየተከሳከስን ሞትን ልናነግስ የምንችልበትን እድል ዘግቷል፤ ኢትዮጵያንም ጠብቋል። የሞት አደጋ አንዣቦባት የነበረችዋ ኢትዮጵያ በንጉሰ ነገስቱ የምህረት አዋጅ ልትድን ችላለች። ያ ዘመን በወንድማማቾች መካከል በሚነሳ ጠብ ደም እንዳይፈስ ዋሽተህም ቢሆን አስታርቅ የሚባልበት ዘመን ነበር። ይህ ቅዱስ የአባቶቻችን የሞራል ስልጣኔ ዛሬ ግን እድሜ ለግራ ፖለቲከኞቻችን በወንድማማቾች መካከል ትብብር እንዳይኖር ዋሽተህ አጣላ በሚል ተተክቷል።*

*ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የምህረት አዋጁን ተጠቅመው የመሰረቱትን የብሔራዊ እርቅ መንግስት የሚነቅፉ አንዳንድ ሰዎች ንጉሰ ነገስቱን አርበኞችን አሸሽተው ባንዳዎችን እንደሾሙ በማስመሰል ይከሷቸዋል። የዚህ ክስ መነሻ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የብሔራዊ እርቅ መንግስት መመስረታቸው ነው። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የብሔራዊ እርቅ መንግስት ውስጥ አርበኞች፣ ግዞተኞች፣ ስደተኞችና ባንዶች ተካተው ነበር። የብሔራዊ እርቅ መንግስት ጽንስ ሀሳብና አሰራር ኔልሰን ማንዴላ «የብሔራዊ እርቅ መንግስት መስራች» ተብለው የኖቬል የሰላም ተሸላሚ ከመሆናቸው ከሀምሳ አመታት በፊት ባገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በታላቁ ንጉሰ ነገስት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስራ ላይ ውሎ ነበር። ንጉሰ ነገስቱ «አርበኞችን አሸሽተው ባንዶችን ሾሙ» በሚል ደርግና ወያኔ ክስ የሚያቀርቡባቸው ኔልሰን ማንዴላ ከሀምሳ አመታት በኋላ ተመሳሳይ የብሔራዊ እርቅ መንግስት መስርተው የኖቬል ተሸላሚ በሆኑበት ተግባር ነው።*

[20] *ደጃዝማች ከበደ ተሰማ፤ የታሪክ፡ማስታወሻ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፤ ፲፱፻፹፪ ዓ.ም. ገጽ ፫፻፺፬*

ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የብሔራዊ እርቅ መንግስት ሲመሰርቱ ራስ አበበ አረጋይን፣ ራስ መስፍን ስለሺን፣ ደጃዝማች ጸሀዩ እንቁ ሥላሴን፣ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን፣ ደጃዝማች ነጋሽ በዛብህንና እና ሌሎች ጀግኖችን ከአርበኞች፤ እነ ሀዲስ አለማየሁን፣ ቢተወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት፣ ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴን፣ ልዑል ራስ መንገሻ ስዩምንና መሰል ሰዎችን ከግዞተኞች፤ መኮንን ኃብተወልድን፣ አክሊሉ ኃብተወልድን፣ ጸሀፌ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሀንስን፣ አብይ አበበንና መሰል ምሁራንን ከስደተኞችና ገብረወልድ እንግዳ ወርቅንና አምደሚካኤል ደሳለኝን አይነት ከዳተኞችን ደግሞ ከባንዶች በማካተት የብሔራዊ እርቅ መንግስት መሰረቱ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የብሔራዊ እርቅ መንግስት ከመሰረቱ በኋላ ጀግኖች አርበኞች ለናት አገራቸው ለዋሉት ውለታ ማዕረግና ማበረታቻ ሰጥተዋቸዋል፣ ለፈጸሙት ጀብዱም ለኑሯቸው ማደላደያ የሚሆን መሬትና ንብረት ሸልመዋቸዋል። የአርበኞች ስም እንዳይጠፋም ለእንደነ ኃይለ ማርያም ማሞ፣ ሽመልስ ሐብቴ፣ በየነ መርዕድ፣ በቀለ ወያ፣ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጋሪ፣ ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ወዘተ. . . አይነት ጀግኖችን መታሰቢያ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎችንና ሌሎች ተቋማትን ሰይመውላቸዋል፤ በስም ላልተጠቀሱ አርበኞች ደግሞ በአንድ ላይ የአርበኞች ትምህርት የሚባል ትምህርት ቤት በመክፈት ስማቸው እንዲጠራ አድርገዋል። የአርበኛ ልጆች እንዲማሩም የአዲስ አበባውን መድህኒያለም ትምህርት ቤት ከፍተው እንደ ፊታውራሪ ወርቁ ስንቄ ልጅ እንደ ስመጥሩ ኳስ ተጫዋች እንደ መንግስቱ ወርቁ አይነት የአርበኛ ልጆችን እንዲማሩ አድርገዋል። የአርበኞቹ ጀብዱ በያመቱ እንዲዘከሩም «የጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር» አቋቁመውላቸዋል።

ወያኔና ደርግ ግን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለጀግኖች አርበኞች የሰጡትን መሬት ቀምተዋቸዋል፤ በእርጅና ዘመናቸው መጦሪያ ይሆናቸው ዘንድ የቋጠሩትን ሀብታቸውን ዘርፈውና ቤታቸውን ወርሰው በግፍ ረሽኗቸው፤ ንጉሱ ያቆሙላቸውን መታሰቢያ አጥፍተውባቸዋል። ደርግ በግፍ ከረሸናቸው ስድሳዎቹ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባለስልጣናት መካከል አብዛኛዎቹ አርበኞች ነበሩ። ከደርግ የተረፉትን ደግሞ ወያኔ ከነ አሻራቸው አጥፍትቷቸዋል። ናዝሬት የነበሩትን በጀግናው አርበኛ ኃይለ ማርያም ማሞ ስም የተሰየመ ትምህርት ቤትና ሆስፒታል አጥፍቶ አዳማ ትምህርት ቤትና አዳማ ሆስፒታል ብሎ ቀይሯቸዋል። ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኋላ የመጡት ሁለቱም ኮምኒስታዊ አገዛዞች ጀግኖች አርበኞቻችን በጦር ሜዳ ጀብዱ ሰርተው ያገኙትን እንደ

ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ወዘተ አይነት አገርኛ ማዕረጎቻቸውን በሙሉ አጠልሽተው «ፊውዳል» የሚል የወል መሳደቢያ ስም በመለጠፍ እንዲያፍሩ አድርገዋቸዋል።

ከፍ ብዬ ካቀረብሁት ማስታወሻ ንጉሰ ነገስቱ አርበኞችን እንዴት እንደሾሙ፤ እንዴት እንደሸለሙና እንዴት መታሰቢያ እንዳቆሙላቸው፤ ከሳቸው በኋላ የመጡት ሁለት አገዛዞች ግን እንዴት አድርገው የአርበኞችን መሬት፣ ቤት፣ መጦሪያና መተዳደሪያ እንደወረሱ፤ እንዴት አድርገው እንደረሸኗቸው፤ እንዴት አድርገው መታሰቢያቸውን እንዳጠፉትና ባጠቃላይ የአርበኛ ጠላት ማን እንደሆነ ማየት የቻላችሁ ይመስለኛል።

እንግዲህ! ከንጉሰ ነገስቱ መውደቅ ጋር ተያይዞ የመጣንበት የቁልቁለት መንገድ እዚህ አድርሶናል። የኢትዮጵያ የቁልቁለት መንገድ ገና አላቆመም። ከአጼው ዘመን ተነስተን እካለንበት ዘመን ያለውን ሁኔታ ላጤነ የመጣንበትን የቁልቁለት መንገድ ለመገንዘብ አዳጋች አይሆንም። ዛሬ ያለውና መለስ ዜናዊ የገነባው የሽፍታ ስርዓት ወራሾቹ «የመለስ ራዕይ» ብለው በሚጠሩት የግለሰብ ቤት፤ የህዝቦችን የመኖር ህልዉናና ሀገር ከማፍረስ የዘለለ ፋይዳ በሌለው የጥፋት መመሪያ እየተገፋ ዛሬ ላይ ግማሽ ህይወቱ ወደ ሞት ተለውጦ እውር ድንብሩን እየሄደ ከሚገኝበት የፍጻሜው አጋማሽ ላይ ደርሷል።

ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ቤተ መንግስታቸውን ሳይቀር የድሀ ልጅ መማሪያ አድርገው ቤት ሰርተው ሲወጡ፤ «ከትልቅ ተወለድ» በሚባልበት መሳፍንታዊ ማህበረሰብ ውስጥ አድገው የገበሬ ልጆችን እነ ገብረየስ ቤኛን ግን «ከትልቅ ሳይሆን ከስራ ተወለድ» ብለው ያስተማሩ፤ «ንጉሱ ይውረዱ!» ብለው ግርግር በማስነሳት ንብረት አውድመዋል ተብለው ከትምህርት ገበታቸው እንዲሰናበቱ የተወሰነባቸውን ተማሪዎች «እየተማሩ ንብረት ካወደሙ፤ ከትምህርት ቢታገዱ ምን ያህል አጥፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሳታመዛዝኑ እንዴት እንዲባረሩ ወሰናችሁባቸው?» ብለው የተባረሩ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ አደረጉ፤ ከወርቅ ህዝብ ተፈጠርሁ የሚለው መለስ ዜናዊ ግን በወያኔ ፕሮግራም የተጻፈውን መብታቸውን የጠየቁ 300 የኦሮሞ ተማሪዎችንና በርካታ የዩኒቨርሲቲው ነባር መምህራንን ንብረት አውድመው ሳይሆን ያይናቸው ቀለም ስላላማረው ብቻ ከትምህርትና ከስራ እስከወዲያኛው ድረስ አሰናብቷቸዋል።

ንጉሰ ነገስቱ ልጆቻቸውንና የድሀ ልጆችን ባገር ቤት አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ እኩል አድርገው አስተምረው ወደ ውጭ ሲልኩ «የምናስተምራችሁ አገራዊ ድህነትን ለማጥፋትና ልጆቻችሁ ድህነት

በሌለበት ሰላማዊት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖሩ ነው» እያሉ ድሀው ወገናችን የህይወትን ሙሉ ጠዓም እየተጎነጨ ከድህነት ወጥቶ የሚኖርባት አገር እንዲፈጥሩ የሚያስችላቸውን እውቀት እንዲገበዩና እንደሳቸው የማትሞተውን ኢትዮጵያ ለማገልገል በሰላም ወደ አገራቸው ተመልሰው የወገናቸው ረዳት እንዲሆኑ እንግዚያብሔርን እንደሚለምኑላቸው ቃል ሲገቡ፤ መለስ ዜናዊና ተከታይ ጀሌዎቹ ግን በአዛውንትነት ዘመናቸው ዘጠና ዘጠኝ በመቶ የሚሆነውን የድሀ ኢትዮጵያውያንን ደም በመምጠጥ ካገሪቱ በላይ ሀብታም ሆነው በዘረፉ ያከማቹትን የምስኪን ኢትዮጵያውያን አንጡራ ሀብት አውሮፓ፣ አሜሪካና ኤስያ በሚገኙ ባንኮች በልጆቻቸውና በመላ ዘመዶቻቸው ስም ሳይቀር ሲያስቀምጡ፤ ልጆቻቸው ከድሀው ተለይተው ምስኪኑን ኢትዮጵያዊ ተጠይፈው ቅንጦት ሳይለያቸው የተቀማጠለ ኑሮ እየኖሩ፤ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በሚገኙ ቁጥር አንድ መዝናኛዎች ሽርሽር እያደረጉ የሚኖሩበትን አለም ለልጆቻቸው ብቻ ሲያመቻቹ፤ «ለተራው» የኢትዮጵያ ህዝብ ግን በርሀብ አለንጋ እየተገረፈና ርስበርስ እየተከሳከሰ ሞትን በማንገስ የሚያልቅበትን፤ ቢታመም ታክሞ የማይድንበትን፤ እንደሰው ሊኖር የማይችልበት ዘግናኝ የድህነት ደረጃ ላይ ደርሶ በችጋር እየተጠራሞተ የሚሞትበትን የአለም የመጨረሻ ድሀና የወደቀች አገር ፈጥረውለታል።

እንግዲህ! ቀደም ብዬ በሳልሁላችሁ የሀሳብ ተዋረድ ሳንመረምር የተቀበልናቸውን የግራ ፖለቲካ ደዌዎች የት እንዳደረሱን፤ በእነዚህ ደዌዎች እየታመምን ከየት ተነስተን የት እንደደረስንና አድሀሪውና ተራማጁ ማን እንደነበር ያያችሁ ይመስለኛል። ዛሬ ላይ ሆኖ ወደ ኋላ ለተመለከተ ከአርባ ሁለት አመታት በፊት የነበረችዋ ኢትዮጵያ የሚሰፋ ድንኳን እየሰራች የነበረች፤ ከኤርትራ እስከ ቦረና ከጅግጅጋ እስከ ጋምቤላ ህበረ ብሔሮቿን እየሰበሰበች፣ በግብርና ስራ እየዘመነች፤ በኢንዱስትሪ እየጎለበተች፤ በየሞያው አስፈላጊውን የሰው ኃይል በሀገር በሀገር ውስጥና በውጭ አገራት እያሰለጠነች በመጓዝ ላይ የነበረች አገር ነበረች። እ.ኤ.አ. በ1960 ኢ.ም. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ምርት የነፍስ ወከፍ ድርሻ ከዩናይትድ ስቴትስ አጠቃላይ የነፍሰ ወከፍ ድርሻ [GDP per person or GDP per capita relative to the United States] አኳያ ሲነጻጸር 1/ 32 [አንድ ሰላሳ ሁለተኛ] ነበር። እ.ኤ.አ. በ2011 ኢ.ም. የኢትዮጵያ አጠቃላይ ምርት የነፍስ ወከፍ ድርሻ ከዩናይትድ ስቴትስ አጠቃላይ የነፍሰ ወከፍ ድርሻ አኳያ ሲታይ ግን ወደ 1/ 60 [አንድ ስድሳኛ] ወርዷል።[21]

---

[21] *Charles I. Jones, 2015. "The Facts of Economic Growth," NBER Working Papers 21142, National Bureau of Economic Research, Inc. PP.40.*

እንግዲህ! ከፍ ብዬ በከፊል የዳሰስኳትን የንጉሰ ነገስቱ ኢትዮጵያ ሳቀርብ ተሰርታ ያለቀች፤ አልጋ በአልጋ እንደነበረች ለማሳየ አይደለም። ሆኖም ግን ያች የንጉሰ ነገስቱ ኢትዮጵያ ጠንካራ ተቋማትን ልንገነባባቸው የምንችላቸው እሴቶችና እርሾ የነበራት፤ ችግር ሲያጋጥማት እንደ ወያኔና ደርግ በደመ ነፍስ ሳይሆን መዋቅራዊ በሆነ መልኩ በተቋማት ለመፍታት የሞከረች አገር ነበረች። በውሸትና በሸፍጥ ተነስተን የመጣንበት መንገድ ግን ዛሬ ወድቀን ከምንገኝበት ደረጃ ላይ አድርሶናል።

## 3. ያለፉት አርባ ሁለት አመታት የመጣንበት መንገድ በአማራ ላይ ያስከተለው መከራ

ዛሬ ወድቃ የምትገኘው የወያኔዋ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ከሚባሉና የራሳቸውን የጸና መንግስት መስርተው በሕዝብ አስተዳደርና በሥልጣኔ ረገድ ቀደምት ከነበሩት አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን፤ ከሶስት ሺህ ዘመን በላይ የታወቀ ክልል፤ መንግስትና ለሌላው አለም ሊተላለፍ የቻለ የሥልጣኔ ምንጭ የነበራት አገር ነበረች። በኢትዮጵያ ረጅም የታሪክ ዘመን በየጊዜው ስልጣን በያዘው የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግስታት ውስጥ በአስተዳደር ሥልጣንና በየሥራ ድርሻውም ሁሉ እንደወቅቱ ሁኔታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሔረሰብ፣ ነገድና ጎሳ የተካፈሉበት ስለመሆኑ ማስረጃ የሚያሻው አይደለም።

ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ሙሉ በመዘዋወር የአገራቸውን ዳር ድንበር ለማስጠበቅ በየጠረፉ ሲንከራተቱ ከኖሩት የኢትዮጵያ ነባር ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል አማራው አንዱና ግንባር ቀደሙ ነው። አማራው በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ ውስጥ ከውልደት አንስቶ እስከ እድገት፤ ለአቅመ ፖለቲካ ከበቃበት የእድሜ ዘመኑ ጀምሮ ግብዓተ መሬቱ እስኪፈጸም ድረስ በኢትዮጵያዊነት ጸንቶ የኖረ ታላቅ ህዝብ ነው። አማራው በኢትዮጵያዊነት ጸንቶ እንደኖረ አገር ወዳድ ህዝብ፡ ባራቱም አጽናፍ ለሚኖረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ሁሉ እኩል አመለካከትና ግምት አዳብሮ ትናንትናም ሆነ ዛሬ ያለውን ለወገኑ አካፍሎ የኖረና የሚኖር ህዝብ ነው። አማራው በኢትዮጵያ በነበሩት የአገዛዝ ስርዓቶች ሁሉ እንደ ሌላው ኢትዮጵያዊ ለማዕከላዊ መንግስት በእኩል ርቀት ላይ የነበረ እንጂ በተለየ አኳኋን እንዲቀርብ ተደርጎ የኖረ ተጠቃሚ እንዳልነበር በቀየው ከሌሎች ህዝቦች ያነሱ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ መንገዶች፣ ኢንዱስትሪዎች መገኘታቸው በቀላሉ አስረጂዎች ናቸው።

ሆኖም ግን ካለፉት ሀያ አምስት አመታት ወዲህ ጣሊያን ጀምሮ የተወውን ኢትዮጵያን በጎሳና በመንደር የመከፋፈል አባዜ የተከተሉ ኮምኒስት ወያኔዎች ባቀናበሩት በአዲሱ የኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ አማካኝነት ረጅሙ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአማራ የበላይነት ተፈርጆ ቀደም ብዬ እንዳቀረብሁት

በአማራው ላይ ያልፈጠረ የሐጢዓት ክስና ያልደረተ የፈጠራ ታሪክ የለም። ወያኔዎች ባቀናበሩት በአዲሱ የኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ መሰረት አማራው ሌላውን ኢትዮጵያዊ በድሏል፤ ጨቁኗል፤ ገዝቷል፤ ወደ ደቡብ የአገራችን ክፍል ለወረራና ለዘረፋ ሄዷል፤ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በወሎና በሸዋ የሚኖረው ደግሞ ጨቋኝና ተጨቋኝ ተብሎ እንዲከፋፈልና እርስ በርስ እየተበላላ እንዲኖር የእልቂትና የውርደት በር ሲከፈትለት ኖሯል።

የትግራይ ሽፍቶች ባቀናበሩት በአዲሱ የኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ መሰረት አማራ የሆኑ አገር አውል አባቶችና ጎልማሶች በረጅም ጊዜ የሥራ ልምዳቸውና እውቀታቸው ያገኙትን አስተሳሰብ ለወገናቸው እንዳያካፍሉ አድሐሪ፣ ትምክተኛ፣ ነፍጠኛ፣ የድሮ ስርዓት ናፋቂ፣ ወዘተረፈ. በሚል የኮድ ስም ጥላሸት እየተቀቡ ከአገራዊ መዓድ ሁሉ የተገለሉ እንዲሆኑ ተደርገዋል። ዘረኞቹ ወያኔዎች ባቀናበሩት በአዲሱ የኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ መሰረት «አማራው በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳታፊ ከሆነ የፖለቲካ የበላይነትንም ይይዛል» በሚለው መርህቸው አምራቹን የአማራ ገበሬ መሬቱን ቀምተውታል።

የትግራይ ኮምኒስቶች ባቀናበሩት በአዲሱ የኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ መሰረት ተምረዋል፤ የቅርቡንና የሩቁን ሁኔታ አገናዝበው አገር የሚያውል ሀሳብ ሊያመነጩ ይችላሉ፤ የተባሉ አማሮች የመዋቅር ማስተካከያ [Structural adjustment] በሚል ከየሥራ ቦታቸው በግፍ እንዲባረሩ ተደርገው እየተወነጀሉና ስም እየተሰጣቸው እንዳይናገሩ፣ አስተያየት እንዳይሰጡና በሙሉ ልባቸው ለአካባቢያቸውና ለአገራቸው እድገት እንዳይሰሩ ተደርገዋል። የአማራን የዘር ማጥፋት ፖለቲካቸው ያደረጉት ወያኔዎች ባቀናበሩት አዲሱ የኢትዮጵያ የመቶ አመት ታሪክ መሰረት የተፈጠረችዋ የወያኔዋ ኢትዮጵያ አማራ የሆነ የማይደመጥበት፤ ታሞ የማይድንበት፤ ህጻን የማያድግበት፤ በጠራራ ጸሐይ የሚገደልበትና ገዳዩ የሚሸለምበት አገር ሆናለች።

ባለፉት 25 የወያኔ የአገዛዝ አመታት አማራው በሚኖርበት ያባቶቹ አገር ሁሉ "ነፍጠኛ" እና "ትምክተኛ" እየተባለ ያልተማረው ምስኪን ገበሬ አማራ ስለሆነ ብቻ በገዛ አገሩ ወደ አገርህ ካልሄድህ ተብሎ ከተራራ ላይ ተወርውሯል፤ በእሳት ተቃጥሏል፤ ለሙና ነባሩ ያባቶቹ መሬት ያንተ አይደለም ተብሎ ከአማራ አንጻር ተካልሏል፤ ከነ ነፍሱ በማይሞላ ገደል ተጥሏል፤ ዘሩ እየተጠራ ተሰድቧል፤ የዘር ማጥፋት ማደኛ ወጥቶበታል፤ ከቁጥር ሳይገባ አሀዙ እንዲያንስ ተደርጓል፤ እንዳይራባ የሚያመክን መርፌ ተወግቷል፤ ዘሩን እንዳይተካ ተኮላሽቷል፤ በአለም ላይ የመጨረሻ ድህ በተባለ ክልል ውስጥ እንዲኖር ተፈርዶበታል፤ በትምህርት ቤት ሳይቀር ነፍጠኝነትን፣ ትምክህትንና በዝባዥነትን ለመስተማር በምሳሌነት ቀርቦ እንደ አደገኛ ርዕዮተ አለምም ብሔረሰቦች ሁሉ እንዲፋለሙት ተዘምቶበታል፤ ብሔርተኞች ሁሉ ባተሌውን የአማራ አርሷደር ባሪያ ፈንጋይና በዳይ አድርገው እንዲቆጥሩት ተደርጓል፤ ትምህርት ቤት የገቡ ህጻናት ልጆቹ

ሳይቀር ከጣራ በላይ በሚጮኸው የብሔርተኞች የውሸት ፕሮፖጋንዳ ጫናና ብዛት የተነሳ የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማቸው ተደርገዋል፤ ከ2.4 ሚሊዮን በላይ አማራ ጠፍቷል። ባጭሩ ዛሬ አማራ የሚኖረው ከፋሽት ጥሊያን በላይ የከፋው የትግሬ ነጻ አውጭ ግንባር ባበጀለት የቁም መቃብሩ ውስጥ ነው።

ምንም እንኳ አማራው ላለፉት ሀያ አምስት አመታት በተለያዩ አደረጃጀቶች ውስጥ እየገባ ፖለቲካው የአማራውን ዘር ማጥፋት የሆነውን ፋሽስት ወያኔን ሲታገል የኖረ ቢሆንም ታላቁ ሰው ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ከመሰረቱት መዐህድ ውጭ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአማራነት ተደራጅቶ የተጠናከረ የፖለቲካ ትግል የሚያካሂድ የረባ የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም። ሆኖም ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአማራነቱ እየተበደለ አንድ ትውልድ የሞላው የኔ ዘመን አዲሱ የአማራ ትውልድ ወያኔ ካበጀለት የቁም መቃብር መግነዙን ቀዳዶና በጣጥሶ የተጫነበትን የመቃብር ድንጋይና አፈር ፈነቃቅሎ ተነስቶ እየተጋደለ ይገኛል። አዲሱ የአማራ ትውልድ ዛሬ ላይ እያደረገው ያለው ያለመጥፋት ተጋድሎ እንጂ እንደ ወያኔ በዘር ተደራጅቶ የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ትግል አይደለም።

በአማራና በወያኔ መካከል ያለው ግንኙነት በተበይና በበይ ወይንም በተገዳይና በገዳይ መካከል ያለ ግንኙነት ነው። ይህንን የምትጠራጠሩ ወያኔ በታህሳት 1968 ዓ.ም. የጻፈውን ፍኖተ መርህ ወይንም ማኒፌስቶ መመልከት ትችላላችሁ።[22] በዚህ ማኒፌስቷቸው ወያኔዎች የትግራይ ህዝብ ትግል ጸረ አማራ ብሔር እንደሆነ በግሏጭ አስፍረዋል፤ በዘፈኖቻቸው «ገረብ ገረብ ትግራይ፣ መቓብር ኣምሐራይ፤» ብለው ዘፈውነዋል። በአማርኛ «ገረብ ገረብ ትግራይ፣ መቓብር ኣምሐራይ፤» ማለት የትግራይ ተራሮች የአማራ መቃብር ይሆናሉ ማለት ነው። «አማራን ቁረጠው» ፤ አማራን አባረው»፤ ወዘተ. . . በሚል በትግሉ ዘመን ብቻ 37 የዘፈን ካሴቶች ሰርተዋል፤ ከ1967 እስከ 2007 ዓ.ም. ድረስ 300 የሚሆኑ ጸረ አማራ ድርሳናትን በትግርኛ፣ በአምርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ጽፈዋል። እነዚህ ሁሉ ለትውልድ የሚሸጋገሩ ድርሳናት በአማራው ላይ የዘር ፍጅት እንዲካሄድ የሚቀሰቅሱ ናቸው። ባለፉት ሀያ አምስት አመታት በአማራው ላይ የተፈጸመው ግፍና በደል እንዲሁም የዘር ማጥፋት ወንጀል የተካሄደው በነዚህ መጽሀፍትና የጥበብ ውጤቶች ማኑዋልነት ነው።

ወያኔዎች በረሀ የገቡት በአማራ መቃብር ላይ የታላቋ ትግራይን ሪፑብሊክ የመመስረት አላማ ይዘው ነው። ሆኖም ግን ኋላ ላይ የምስራቁ አለም እየተዳከመ ሲሄድና የምዕራቡ አለም ቀዝቃዛውን ጦርነት

[22] *TPLF, Manifesto of the Tigray People's Liberation Front, vol. 1, February 1976.*

እያሸነፈ ሲመጣ፤ ደርግ ወድቆ ሻዕብያን ተከትለው አዲስ አበባ እንደሚገቡ ሲያውቁት፤ አማራን ለማጥፋት ከ1967— 1981 ዓ.ም. የታገሉበትን ፍኖተ መርህ በግንቦት ወር 1981 ዓ.ም. ቀይረው «ኢህአዴግ» የሚባለውን የማታለያ ጭንብል መስርተው ጫካ ሲገቡ ያነገቡትን አማራን የማጥፋት አላማቸውን በመንግስትነት ከተሰየሙ በኋላ ለማስፈጸም የተነሱለትን አማራን የማጥፋት አላማ ወደ ርዕዮተ አለም ደረጃ ከፍ አድርገውታል። ይህንን ርዕዮተ አለም መለስ ዜናዊ « አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ሲል ይጠራዋል።

አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚባለውን የመለስ ዜናዊ ርዕዮተ አለም ከፍቶ ለተመለከተ የርዕዮተ አለሙ ዋና ማዕከሉ ወይንም coreሩ የአማራ ጥላቻና አማራን የማጥፋት ነው። ባለፉት ሀያ አምስት የፋሽስት ወያኔ የአገዛዝ አመታት ውስጥ በአማራ ላይ የተፈጸመው ግፍና በደል ባጋጣሚ የተከሰተ፤ የአማራ የአይን ቀለም ስላላማረ የተፈጸመ ድርጊት አይደለም። ይልቁንም ይህ በአማራ ላይ የተፈጸመው ግፍና በደል ታሪካዊ መነሻ ያለው፤ ተቋማዊ ቅርጽ የተሰጠውና በርዕዮት አለም የታገዘ ግፍና በደል ነው። ታሪካዊ መነሻውን[23] ለጊዜው ልተወውና የፋሽስት ወያኔ የአማራ ማጥፊያ የፖለቲካ ርዕዮተ አለም መሰረት የሆነውን አብዮታዊ ዲሞክራሲን ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ልገልጸው እፈልጋለሁ።

አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚባለው የወያኔ ርዕዮተ አለም የሌኒን ፍልስፍና ሲሆን በባህሪው ያዳላል። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ዲሞክራሲያዊ አይደለም። አብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚነሳው ዲሞክራሲና የሕግ ከለላ የሚገባቸውና የማይገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አሉ ብሎ በማሰብ ነው። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እነዚህ መብቶች አይገባቸውም የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ወይ «በዘር» አልያም «በመደብ» ይለያሉ። ቀደም ብዬ የነገርኳችሁ የአማራ የበላይነት፤ አማራ ነፍጠኛ፤ አማራ ጨቋኝ፤ ወዘተ የሚባሉት ስያሜዎች በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አማራውን ለማጥፋት የተፈጠሩ ጦርና ጋሻዎች ናቸው።

የወያኔ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ደርግ በሚያዚያ ወር 1968 ዓ.ም. ይፋ ካደረገው የኢትዮጵያ አብዮት ፕሮግራም ወይንም National Democratic Revolution (NDR) program ጋር አንድ አይነት ነው። የሁለቱ አገዛዞች ርዕዮተ አለም ማህደር የካርል ማርክስ Dictatorship of the Proletariat ወይንም የወዝ አደሩ አምባገነንነት የሚለው አስተምህሮ ነው። የሁለቱ አገዛዞች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ልዩነት በደርጉ የኢትዮጵያ አብዮት ፕሮግራም ዲሞክራሲ አይገባውም የተባለው የህብረተሰብ ክፍል በመደብ ሲለይ [ ደርግ «ፊውዳል፣ ባላባት፣ በዝባዥ፣ አብዮት ቀልባሽ» የሚላቸውን ማለቱ ነው] የወያኔው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ደግሞ ዲሞክራሲ አይገባውም የተባለው የህብረተሰብ ክፍል በኮድ ስም ትምክህተኛ፣ የድሮ ስርዓት ናፋቂ፣ ወዘተ ተብሎ የተለየ ሲሆን ወያኔ ግን እነዚህን የኮድ ስሞች የሚጠቀመው ዲሞክራሲ አይገባውም የሚለውን ክፍል በቀጥታ አማራ ላለማለት ነው።

---

23 *ብርሀኑ አስረስ፤ ማን ይናገር የነበረ ፤ የታኅሣሡ ግርግርና መዘዙ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ 2005 ዓ.ም. ገጽ 189.*

ባጭሩ ወያኔ ዲሞክራሲ አይገባውም ብሎ የመደበው የህብረተሰብ ክፍል የተለየው በዘር ሲሆን ያ ዘር ደግሞ ወያኔ ከምስረታው ጀምሮ ሊያጠፋው የተነሳው የአማራ ዘር ነው። በዚህም የተነሳ ደርግ ከ1967—1983 ዓ.ም. «ፊውዳል፣ ባላባት፣ በዝባዥ፣ አብዮት ቀልባሽ» በሚላቸው ላይ ቀይ ሽብር አውጆ ካካሄደው ጅምላ ግድያ የከፋ አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ወያኔ ባለፉት ሀያ አምስት አመታት በአማራ ላይ ፈጽሟል። በዘመነ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አማራው ዲሞክራሲ አያስፈልገውም በመባሉ በአገሩ አገርህ ሂድ ተብሎ ከተራራ ላይ ተወርውሯል፤ ቤት ተዘግቶበት በእሳት እንዲቃጠል ተደርጓል፤ ከነሰፍሱ በማይሞላ ገደል ውስጥ ተጨምሯል፤ ዘሩን እንዳይተካ የአማራ ሴቶች የሚያመክን መርፌ ተወግተዋል፤ የህግ ጥበቃ፣ ስራ የማግኘትና የትምህርት እድል ተነፍጓል፤ የንብረት መብት፣ ያለመፈናቀልና የመኖር መብቱ በግላጭ ተገፏል።

አማራው በፋሽስት ወያኔ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ዲሞክራሲ አያስፈልገውም በመባሉ ግብር ከፍሎ በሚያስተዳድረው በራሱ መገናኛ ብዙሀን ሳይቀር ሀያ አምስት አመት ሙሉ በህዝብ ተመረጥን እያሉ በሚደሰኩሩ፤ ኃላፊነት ሊሰማቸው በሚገባ የፖለቲካ መሪዎች፤ ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛና በዝባዥ በሚሉ የኮድ ስሞች እንደ አደገኛ ርዕዮተ አለም ሁሉም እንዲፋለሙት ተዘምቶበታል። ይህ ዘመቻ ዛሬም አልቆመም። ከአንድ ወር በፊት የትግራዩ ገገር በትግርኛ ባደረገው ንግግር «ጎንደር ላይ የተፈጸመውና በትግሬዎች ላይ የተካሄደው ተግባር ምንጩ ትምክህተኝነት ነው። ይህንን ትምክህት ከስሩ ለመንቀል ያቺን ተንከሲስ እያመረተች የምትልክ ጉድጓድ መድፈን አለብን።» ሲል በይፋ በአማራ ላይ ቀይ ሽብር አውጇል። ዛሬ ዛሬ ድምጸ ወያኔና «የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን» በተለይም የትግርኛው አገልግሎት እንደ ሩዋንዳው ሬዲዮ ሚሌ ኮሊንስ ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ ዝቅተኛውን የጋዜጠኝነት መስፈርትን በማያሟላ አኳኋን አፍራሽ በሆነ ፕሮፓጋንዳ ተጠምዶ በአማራ ላይ የዘር ማጥፋትና እልቂት እንዲካሄድ ቤንዚን እያርከፈከፈ ይገኛል።

በፋሽስት ወያኔ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አማራው ዲሞክራሲ አያስፈልገውም ተብሎ ስለተደመደመ፣ ለንብረቱም ሆነ ለህይወቱ ጥበቃ አያስፈልገውም ስለተባለ ወያኔ ባመነው እንኳ 2.4 ሚሊዮን አማራ ጠፍቷል። ይህ አሀዝ የቁጥር መቀነስ ነው ተብሎ ቢወሰድ እንኳ የዚህ ቁጥር መቀነት በበጀት ምደባ ላይ የሚያመጣው ጉዳት በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድ፣ በግብርናና በሌሎችም የአስተዳደር ጉዳዮች ላይ አማራ የሚገባውን እንዳያገኝ ማድረጉ ግልጽ ነው። በፋሽስት ወያኔ አብዮታዊ ዲሞክራሲ አማራው ዲሞክራሲ አያስፈልገውም በመባሉ በርዕዮተ አለም የታገዘ፤ ስልታዊ [systematic] የሆነ፤ በተለያዩ ነገሮች ወደፊት እንዳይሄድ እልቆ መሳፍርት በደልና ግፍ ተፈጽሞበታል።

ባጭሩ ከ1967 ዓ.ም. እስከ ዛሬ ድረስ ያለው የወያኔ ፖለቲካና የመለስ ዜናዊ የርዕዮተ አለም ፍልስፍና መነሻ በአማራ ላይ የሚፈጸም የዘር ማጥፋት ወይንም በእግሊዝኛው አጠራር Genocide (of the Amharas) ነው

ማለት ይቻላል። ይህንን ስል ብዙ ሰው ለመቀበል ሲቸገር እመለከታለሁ። እስቲ የዘር ማጥፋት ወይንም Genocideን አለማቀፋዊና አህጉራዊ ፍቺውን ትተን በተሻሻለው የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ውስጥ በምን አኳኋን እንደተቀመጠ እንመልከት።

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀጽ 269 ስለ ዘር ማጥፋት ወንጀሎች ምንነት የተብራሩ ዝርዝሮችን አካቷል። አንቀጹ እንደሚከተለው ይቀርባል፤

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ  አንቀጽ 269፡ የዘር ማጥፋት፤

ማንም ሰው በሰላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጎሳ፣ በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለም፣ በኃይማኖት ወይንም በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን በመላ ወይንም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ፣ የጥፋቱን ድርጊት በማደራጀት፣ ትዕዛዝ በመስጠት ወይንም ድርጊቱን በመፈጸም፡-

ሀ) በማንኛውም ሁኔታ የማህበረሰቡን አባሎች የገደለ፤  አካላዊ ወይንም የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይንም ያጠፋ እንደሆነ፤ ወይንም

ለ) የማህበረሰቡ አባላት በዘር እንዳይራቡ ወይንም በሕይወት እንዳይኖሩ ለማድረግ ማንኛውንም ዘዴ በስራ ላይ ያዋለ እንደሆነ፤

ሐ) የማህበረሰቡን አባላት ወይንም ህጻናት በግዴታ ከስፍራ ወደ ስፍራ ያዛወረ ወይንም የበተነ ወይንም ሊሞቱ ወይንም ሊጠፉ በሚችሉበት የኑሮ ሁኔታ እንዲኖሩ ያደረገ እደሆነ የዘር ማጥፋት ፈጸመ ይባላል።

እንግዲህ!  እነዚህን  በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ የተቀመጠጡን የዘር ማጥፋት ወንጀል ዝርዝሮች  ወያኔ ከምስረታው ከ1967 ዓ.ም. እስከ ዛሬ ድረስ  በአማራ ላይ ፈጽሟቸዋል፤ ዛሬም እየፈጸማቸውም ይገኛል።

አንዳንድ ሰዎች የወያኔው የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ 2.40 ሚሊዮን አማራ ጠፋ ያለውን ማስረጃ አንቀበልም ይሉና በአማራ ላይ ተፈጸመ የምንለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ላለመቀበል ሲሟገቱ ይሞክራሉ። ላላስተዋሉትም እንጂ የአማራ ቁጥር በ2.40 ሚሊዮን ጎድሏል የሚለውን «ኦፊሲያላዊ» መረጃ በራሱ «የሞተ ሰው ቁጥር» አይደለም ብለን እንኳ ብንወስድ የአማራ ቁጥር በ2.40 ሚሊዮን ያህል እንዲቀንስ መደረጉ በአማራው ላይ የተፈጸመ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሆነ ማየት ይችሉ ነበር። የአማራ ቁጥር በ2.40 ሚሊዮን ጎደለ ማለት ለአስር አመት [ድጋሚ የቤትና የህዝብ ቆጠራ እስኪካሄድ ድረስ፤ ያውም ድጋሜ

ቆጠራ ሲካሄድ ጠፋ የተባለው 2.40 ሚሊዮን የሚካተት ከሆነ ነው] ያህል 2.40 ሚሊዮን የሚሆን አማራ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የመሰረተ ልማቶች ዝርጋታ፤ ለገጠርና ከተማ ልማት እንዲሁም ለዴሞክራሲና ሰላም ግንባታ የሚውል አመታዊ ባጀት ለአስር አመታት ያህል አልተመደበለትም ማለት ነው። ይህ ማለት 2.40 ሚሊዮን አማራ ለአስር አመት መሰረታዊ የሆኑ ፍላጎቶች ሳይሟሉለት እንዲኖር ተደርጓል ማለት ነው።

መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ያልተሟሉለት ህዝብ ደግሞ በድህነት፣ በርሀብና በችጋር ተጎሳቁሎ ይጠፋል። ስልታዊ በሆነ መልኩ 2.40 ሚሊዮን አማራ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ሳይሟሉለት ቀርተው በድህነት፣ በርሀብና በችጋር ተጎሳቁሎ ሊሞት ወይንም ሊጠፋ የሚችልበትን የኑሮ ሁኔታ እንዲኖር ማድረግ ደግሞ ከፍ ብሎ በቀረበው የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ አንቀጽ 269 መሰረት የዘር ማጥፋት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የዘር ማጥፋት የዘር ማፈናቀል ወንጀልንም ይጨምራል። ላለፉት ሀያ አምስት አመታት ወያኔ «ከአማራ የጸዳ አካባቢ መፍጠር» የሚለውን ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም ሲል አማራ በመሆናቸው ብቻ ከአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች እንዲፈናቀሉና ሜዳ ላይ እንዲወድቁ አድርጓል። ይህ የግፍ ተግባር ዛሬም ቀጥሎ ንብረታቸው የተዘረፈ፤ ደማቸው የፈሰሰ የአማራ አርሶአደሮችን ቁጥር በሚሊዮኖች የሚቆጠር አድርጎታል። ባጠቃላይ ላለፉት ሀያ አምስት አመታት በአማራ ላይ የተፈጸመው ግድና፣ ሰቆቃ፣ መከራ፣ የዘር ማጥፋትና ተያያዥ በደሎች ምድሪቷ ከምትሸከመው በላይ ሆኗል።

የአማራ ዘር ማጥፋት ፖለቲካው በሆነው አገዛዝ ውስጥ የተለመደው አይነት ሰላማዊ ትግል ለማድረግ መሞከር ከጥይት ተርፎ እስር ቤት የሚገባበት እድል ቢገኝ እንኳ እጣ ፈንታው በእሳት መንደድና ገላው በትግራይ ወታደሮች መተልተል መሆኑን የተገነዘበው አዲሱ የአማራ ትውልድ ንቅናቄውን ተጋድሎ አድርጓል።

በዘርና በጎሳ ፖለቲካ መካከል ያልተወከለውና ድምጹን የሚያሰማለት የሌለው የአማራ ህዝብ ድምጹን የሚያሰማለት አካል ባለመኖሩ ቅርጽ በተሰጠው ተቋማዊ የጸረ አማራ ፖለቲካ ውስጥ ለመኖር አዲሱ የአማራ ትውልድ ራሱን አደራጅቶ ለወገኑ ድምጽ ለመሆንና አማራውን ከፈጽሞ መጥፋት ለመታደግ መጠነ ሰፊ ስራዎች በአገር ውስጥና በውጭ አገር እየተሰሩ ይገኛሉ። በአገር ውስጥ ያለው አዲሱ ትውልድ አደረጃጀት አለም ከችጋር፣ ከበሽታና ከድንቁርና ነጻ ወጥቶ፤ ወንጀል፣ እስራት፣ ጭቆና፣ ግፍና የኑሮ ጭንቀት ተረስቶ፤ የሰው ልጆች በፍቅርና በደስታ ምድራዊ ገነት ፈጥሮ እየኖረ ከገነቱ ቀርቶ ከመካነ-ንስሐው ሳይደርስ ወያኔ ባባጀለት ሲኦል ውስጥ ሁኖ ፈጽሞ እስኪጠፋ እየተሰቃየ የሚገኘውን አማራ ለመታደግ <u>የህልውና ተጋድሎ</u> እያደረገ ይገኛል። ይህ ትግል በበይና በተበይ መካከል የሚደረግ ተጋድሎ እንደመሆኑ መጠን ወደፊት እንጂ ወደኋላ በማይሄድበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በዚህም የተነሳ ዛሬ ላይ

ተጋድሎ የደረሰበት ደረጃ  የወያኔን በቅርቡ መወገድ አይቀሬነትና የሽግግር ሂደትን ተገቢነት ከግምት በላይ አድርጎታል። ስለሆነው ቀጣዩ ምዕራፍ  ስለሽግግሩ መሰረታውያን  ውይይት የሚቀሰቀስበት  መሆን ይገባዋል።

## 4. የሽግግሩ ምሰሶዎች ምን መሆን ይገባቸዋል?

ቀደም ብዬ እንዳልሁት ወያኔ ዛሬ ላይ  ግማሽ ህይወቱ ወደ ሞት ተለውጦ እውር ድንብሩን እየሄደ ከሚገኝበት የፍጻሜው አጋማሽ ላይ ደርሶ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ ነፍሱን በጥርሱ ይዞ እየተወራጨ መሪው መንገድ ላይ ጥሎት የሄደ አይነ ስውር ሆኗል። ኢትዮጵያም መስቀለኛ መንገድ ላይ ትገኛለች። ይህንን ከኛ  ከአገር ባለቤቶቹ ቀድመው  የተረዱት ፈረንጆች በተደጋጋሚ  የምትፈርስ አገር ወይንም failed state ሲሉ  የሚያጋጥመንን አደጋ እየነገሩን ነበር።

የሚያጋጫቸው ብሔረሰቦች መከፋፈል የበጃቸው ወያኔዎች የራሳቸውን ህይዎት ካገሪቱ ህይዎት አስበልጠው፤ በምንም አይነት መንገድ ለአገር ብለው የእለታዊ ጥማቸውን ብልጫነት ሳይዘነጉ፤ ስለዚሁ ስለ እለታዊ ጥቅማቸውና ስለ ግል ህይዎታቸው ሲሉ አስራ ሰባት አመታት በዱር በገደል ሲንከራተቱ፤ ለሀያ አምስት አመታት ደግሞ በመንግስትነት ሆነው፤ የትም ወድቀው የቀሩትን የትግራይ ድሀ ልጆች መስዋእትነት ከንቱ በማድረግ፤ የኢትዮጵያን ህዝብ በጎሰኝነት ሞተር እየነዱ በታሪኩ አይቶት በማያውቀው የደህነት አዘቅት ውስጥ ከተውት ከምንገኝበት መስቀለኛ መንገድ ተነስተን መድረሻችን አሁን ያጋመስነው እንደ ሕዝብ የመኖር እጣችን ለጊዜውም ቢሆን ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት አሊያም የሚያቆምበት ደረጃ የምንደርስ ይመስለኛል። ነገሮች በዚህ የሚቀጥሉ ከሆነ ቀደም ብዬ የገለጥሁት እውን ስለመሆኑ የሚጠራጠር ካለ እስካዚያው ብርታቱን ይስጠው እንጅ ወደሜዳው እየዘለቅን ስለሆነ ስንደርስበት ያየዋል።

ዛሬ ላይ ሆኜ የወደፊቱን ሳስብ ሁለት ምርጫዎች ብቻ ያሉን ይመስለኛል።

1. አንደኛው ምርጫ ከነ ሕገ መንግስቱ፣ ከነ መሬት ፖሊሲው፣ ወዘተ. . .  ባለፉት አርባ ሁለት አመታት በተለይም ባለፊት ሀያ አምስት አመታት የመጣንበትን መንገድ የመንግስት ለውጥ አድርጎ በተለየ መንገድ ማስቀጠል ሲሆን፤
2. ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ ቆም ብለን ያለፉትን አርባ ሁለት ዓመታት እንደገና በመገምገም ነገሮችን አመዛዝኖ የተሸወድንባቸውን በመፈተሽ ወዴት መሄድ እንዳለብን ተጨንቀን በማሰብ ከታሪካዊ ችግሮቻችን የምንገላገልበትን ድልድይ መስራት ናቸው።

አንደኛው ምርጫ የመንግስት ለውጥ አድርገን ያለውን ስርዓት በማስቀጠል ባለፉት አርባ ሁለት አመታት በመጣንበት የመከራ አዙሪት እየዳከርን በአይነቱ ልዩ ወደሆነ ሌላ የመከራ አዙሪት የምንዘፈቅበት፤ ለኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ጉዳት የሚያስከትልና በአለም ሁሉ ታይቶና በተግባር ተፈትሾ አውዳሚነቱን አስመስክሮ የከሸፈው አማራጭ ነው። ሁለተኛው አማራጭ የመንግስትም የስርዓትም ለውጥ የምናደርግበትና ከራሳችን ጋር ታርቀን ከታሪካዊ ችግሮቻችን የምንገላገልበት መንገድ ነው።

በሁለተኛው የመፍትሔ ሀሳብ ላይ ትልቅ ችግር የሚሆኑብን የወያኔ ርዕዮተ አለም አራማጆች ይመስሉኛል። በብዛት በተቃዋሚ ጎራ ያሉት የወያኔ ርዮተ አለም አራማጆች ያለፉት አርባ ሁለት አመታት የተሰራውን አስተካክለን እንሂድ እንደሚሉ በርግጠኛነት መናገር ይቻላል። እነዚህ አካላት ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመጣ የሚፈልጉት ለውጥ የመንግስት ለውጥ እንጂ የስርዓት ለውጥ አይደለም። ቋንቋችን በሚሉትን መናገርን፣ የብሔረሰባቸው ስም መታወቂያቸው ላይ መጻፉን፣ ወያኔ በፈቀደላቸው ክልል ውስጥ መኖራቸውን እንደ ትልቅ ለውጥ ስለተቀበሉት የሚፈልጉት ለውጥ ወያኔ በእንደራሴነት ከሾማቸው የብሔረሰባቸው አባላት ከሆኑ የአካባቢያቸው ሎሌዎች «እኛ የተሻለ እንሰራዋለን» ብለው የሚያልሙትን ለማስፈጸም የሚያስችላቸውንና እነሱ የሚሾሙበትን የመንግስት ለውጥ እንጂ የስርዓትን ለውጥ እንዲኖር አይደለም። እነዚህ ሰዎች የግለሰብ መብት የሚገፋ ስርዓት ተይዞ የራስ መንግስትም ቢመሰረት መቼም ቢሆን ወደፊት መራመድ እንደማይቻል የተገነዘቡ አይመስልም። ባጭሩ የወያኔ ርዮተ አለም ወንድሞች የመንግስት ለውጡን የሚፈልጉት የተበላሸው የወያኔ ፕሮግራም [ህገ መንግስት ላለማለት ነው] ጎደለው የሚሉትን ለማስተካከል ነው።

እውነቱን እንነጋገር። ወያኔ በግፍ ዙፋኑ ላይ በተደላደለ ፍራሽ ያለ ስጋት እንዲተኛ ያደረገው ያሰለፈው ወታደርና በእጁ ያለው የጦር መሳሪያ ብቻ አይደለም። ወያኔ በግፍ ዙፋኑ ላይ በተደላደለ ፍራሽ ላይ ያለ ስጋት እንዲተኛ ያደረጉት ከፍ ብዬ የገለጽኋቸው ርዕዮተ አለም አጋሮቹ ጭምር ናቸው። እነዚህ ኃይሎች እንደማን እንደሆኑ ስለሚታወቅ በሥም እንድጠቅስላችሁ የምትፈልጉ አይመስለኝም። መንፈሳዊ ወኔውን አግኝነትን በተለይውም ባለፉት 42 ዓመታት የተፈጠሩትን ችግሮቻችንን ከጥግ እስከ ጥግ ካላየንና እየተነጋገርንበት ያለውን ሽግግር የምንፈልገው በወያኔ ዘመን ብቻ የተፈጥሩ ችግሮቻችን ለማከም ከሆነ በመንግስት ለውጥ ብቻ አይደለም ከገባንበት አዙሪት ልንወጣ ሽጡን መሻገር አንችልም። ባለፉት አርባ ሁለት አመታት ህዝባችን ብዙ መብቶችን አጥቷል። ባለፉት አርባ ሁለት አመታት ህዝባችን መንግስት ወደላይ የሚያይ ሙብት ለማኝ ሆኗል። ራሱን ችሎ ይኖር የነበረው ህዝብ ባለፉት አርባ ሁለት አመታት ለውጥ መጣ ተብሎ ወደ መንግስትና ወደ መንግስተ ሰማያት አንጋጥጦ እንዲያይ ተደርጓል። እየታሰበ ያለው ሽግግር ለዚህ መፍትሔ ማበጀት አለበት። ብቸኛው መፍትሔም የግለሰብ መብት ህገ መንግስታዊ ሲሆን ነው። የሚታሰበው የሽግግር ሂደት ሲጀመር ባለፉት አርባ ሁለት አመታት ህዝባችን ያጣቸውን መብቶች

በማስመለስ መጀመር አለበት። መሬት ላራሹ እንደገና ታውጆ፤ የሁከት ይወገድልኝን አዋጅም ተሰርዞ መሬት የገበሬው የግል ሀብትነት ህገ መንግስታዊ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።

መሬት ላራሹ እንደገና መታወጅ ያለበት ማንም ካድሬ እየተነሳ ገበሬውን ከመሬቱ እንዳይነቅለውና ጭሰኛ እንዳያደርገው ነው። በንጉሱ ዘመን በገበሬው መሬት [በጭሰኛው አላልሁም] ዝር የሚል አልነበረም። ዝር የሚል ቢኖር እንኳ ገበሬው መልስ የሚሰጠው ለአንድ ጭቃ ሹም ብቻ ነበር። ዛሬ ግን ጭሰኛው [ገበሬው አላልሁም] ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ከፍተኛ፣ ወዘተ በሚባሉ እልቆ ቢስ የካድሬ ሰንሰለቶች ሁሉ መልስና መላሾ መስጠት ግዴታ ሆኖበታል። ዛሬ የኢትዮጵያ አርሷደር ከገዛ መሬቱ፤ አያት ቅድሚያ አያቱ ከተወለዱበት መሬቱ ላይ «ልማታዊ ባለ ኃብት መጣ» እየተባለ ከአንጡራ ሀብቱ በልማት ተፈናቃይ ስም በካሬ ጥቂት ሳንቲም ተከፍሎት ይባረራል።

የኢትዮጵያውያን ሽምግልና ባለፉት 42 ዓመታት ከተነጠቅናቸው ዘርፈ ብዙ አገር በቀል ተቋማት አንዱ ነው። ይህ መመለስ ይኖርበታል። አቤ ጉበኛን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግስት እንደ አቤ ጉበኛ የኮነነ የለም። ለኔ አቤ ጉበኛ የመንፈስ አባቴ ነው። አቤን እንደምወደው የምታውቅ እስራኤል አገር የምትኖር ልጁ የአቤን አስገራሚ ፎቶዎች ልካልኝ ነበር። ከላከችልኝ ፎቶዎች መካከል አንዱ ፎቶ አቤ ጣና ዳር ሄዶ ሽጉጡን ታጥቆ የተነሳው ፎቶ ነው። በዚያ ዘመን አቤን የሚያህል ተቃዋሚ ጸሀፊ በአደባባይ መሳሪያ የመታጠቅ መብት ነበረው። እስክንድር ነጋ ወይንም ተመስገን ደሳለኝ ሽጉጥ ታጥቀው አዲስ አበባ ሲዘመዋወሩ ቢገኙ ኖሮ በተገኙበት ይገደሉ ነበር። ከ42 አመታት በፊት ህጋዊ የነበረው የኢትዮጵያውያን መሳሪያ የመታጠቅ መብት [the right to bear arms] ዛሬ በአሸባሪነት የሚያስከስስ አደገኛ ወንጀል ሆኗል። እንደ አሜሪካኖቹ ሁሉ ከራሳ የታረቀችዋ ኢትዮጵያ ህገ መንግስትም የማይነኩና የማይገሰሱ የሙብት ድንጋጌዎች ወይንም Bill of rights ያስፈልጉታል። ባጭሩ እየታሰበ ያለው ሽግግር ቢያስን የተነጠቅናቸውን መሰረታዊ ሙብቶች ማስመለስ አለበት። ያለፉት አርባ ሁለት አመታት ያየናቸው መንግስታዊ ብልግናዎች እንዳይደገሙ ከሽግግሩ በፊት ብዥታ የማጥራት እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ሌላው ሽግግሩ ሊያስብበት የሚገባው ነገር የወያኔ ርዕዮተ አለም ተጋሪዎች የሆኑ ተቃዋሚዎች እንዲስተካከል እንጂ እንዲቀየር የማይፈልጉት የወያኔ ፕሮግራም ጉዳይ ነው። ወያኔዎች ህገ መንግስት ያደረጉት የራሳቸውን ፕሮግራም ስለሆነ ዛሬ «የኛ ፍላጎት» ለማለት ሲፈልጉ ህገ መንግትቱ ይሉናል። ይህ ፕሮግራም የዘረኛነት አዋጅ ነው። የተለያዩ ዘሮች ባሉበት አገር ውስጥ ፖለቲካው የዘር ሆኖ መቼም ቢሆን ፍትሐዊነት ሊኖር አይችልም። የወያኔ ህገ መንግስት ሁለተኛ ዜግነትን ፈጥሯል። ዛሬ ክልሎች የሚባሉት መስተዳድሮች የኀሳ ባለቤቶቹ ናቸው ተብሏል። ወያኔ ለራሱ ፍላጎት ሲል በትክክል ያልተረጎመው ይህ ህገ

መንግስት በትክክል ይተግበር ቢባል እንኳ አግላይ ነው። በክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችን በሙሉ በእኩል አይን አያይም። እንደሚታወቀው ከግማሽ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ እየኖረ ያለው ያንተ አይደለም በተባለ አስተዳደራዊ ክልል ውስጥ ነው። ይህ ማለት ግማሽ የሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የመመረጥ፣ ንብረት የማፍራት፣ በራሱ ቋንቋ የመዳኘት መብት የለውም ማለት ነው። ጅማ የሚኖር ጉራጌ መንግስታዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት በቁቤ መጻፍ ይኖርበታል። ሻሸመኔ የሚኖር ወላይታ ፍርድ ቤት የሚቀርበው በትርጁ ማን ነው። ዛሬ ኦሮምያ በሚባለው ክልላዊ አስተዳደር ውስጥ የሚኖሩ በርካታ ሚሊዮን አማሮች ግብር እየከፈሉ ጨፌ ኦሮምያ ውስጥ አንድም ወኪል የላቸውም። ናዝሬት የሚኖር የጋሞ ሰው ለአዳማ አይመረጥም። ሻሸመኔ የሚኖር ሲዳማ ለሻሸመኔ አይመረጥም። ሀረር የሚኖር አማራ በሀረሬ ክልላዊ መንግስት ውስጥ የመመረጥ፣ ራስን የማስተዳደር መብት የለውም።

ባጭሩ የወያኔ ህገ መንግስት «እኛና ሌሎች» የሚል አስተሳሰብን ፈጥሯል። እኛና ሌሎች የሚለው አስተሳሰብ እስካልተወገደ ድረስ እኩልነትና መብት ሊከበር አይችልም። ስለዚህ ሁለተኛ ዜግነት የፈጠረው የወያኔ ህገ መንግስት መቀየር አለበት። ሽግግሩ «እኛና ሌሎች» የሚለውን አስተሳሰብ አጥፍቶ፤ ዛሬ «ዘርህ ከሌላ ነው» በሚል ሰበብ ሁለተኛ ዜጋ የሆነውን በርካታ ህዝብ የአገሩ ባለቤት የሚያደርግና ሁሉንም በእኩል የሚያስተናግድ ህገ መንግስት ማርቀቅ አለበት። ይህ የሚረቀቀው ህገ መንግስት ምንንም ነገር ታሳቢ ያድርግ የግለሰብ መብትን ግን ከጥግ እስከ ጥግ ማስከበርና ጥበቃ እንዲደረግለት ማድረግ አለበት።

በመጨረሻ ወደፊት የሚታሰበው ሽግግር እንዲፈጽማቸው የምሻቸውን የሚከተሉት ጉዳዮች እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ፤

1. እንደምታውቁት ከዛሬ ሀያ አምስት አመታት በፊት ኢትዮጵያ በክልሎች ስትከፋፈል ከኢትዮጵያ ህዝብ ዋና ከሚባሉት አንዱ የሆነው አማራው አልተወከለም። በርግጥ ያኔ ያልተወከለው አማራው ብቻ ሳይሆን በርካታ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አልተወከሉም። ህዝባዊ ነኝ የሚል የትኛውም የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ዋነኛ ከሚባሉት የኢትዮጵያ ብሔሮች መካከል ዋናው ያልተወከለበትን ህገ መንግስትና የአገር አሸናሸን እንደ ህጋዊና ሞራላዊ ክንዋኔ ሊቀበለው አይገባም። ስለዚህ እየታሰበ ያለው ሽግግር ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚደረግ ከሆነ አማራ ያልተወከለበትን ህገ መንግስትና የአገር አሸናሸን እንደ ፍትሕብዊ ክንዋኔ ሊቆጥር አይገባም። ስለዚህ ሽግግሩ ሥራውን ሲጀምር ይህንን ኢፍትሐዊና ህገ ወጥ ተግባር ውድቅ በማድረግ ህዝባዊነቱን ማሳየት አለበት።

2. በሁለተኛ ደረጃ የማቀርበው ማሳሰቢያ ደግሞ እየታሰበ ያለው ሽግግርም ሆነ ህገ መንግስት የማርቀቅ ሒደት ባለፉት ሀያ አምስት አመታት ውስጥ በአማራው ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል እውቅና እንዲሰጥና እንዲያወግዝ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ያለፉት አርባ ሁለት አመታት በወለደው ፖለቲካ ምክንያት በአማራ ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት፤ ወያኔ በራሱ ያመነውን የ2.4 ሚሊዮን አማራ መጥፋት እንኳ ከታዋቂዎቹ የጉራጌ ተወላጅ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ከአቶ አሊ ሁሴንና ከዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም በስትቀር አንድም የፖለቲካ ሲያወርግዝ አላየሁም። የሆሎኮስትን የዘር ማጥፋት «አልተፈጸመም!» ማለት ወንጀል እንደሆነ ለናንተ አልነግራችሁም። ስለዚህ በአማራ ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል በሽግግሩ ሒደት እውቅና አግኝቶ ተመሳሳይ የዘር ማጥፋት በደል ወደፊት በኢትዮጵያውያን ላይ እንዳይፈጸም የሽግግሩ ሒደት ለዚህ ዋስትና ጥበቃ መስጠት አለበት።

3. ሶስተኛው ቀደም ብዬ ያቀረብሁትና የወደፊቱ ህገ መንግስት ሲረቀቅ የግለሰብ መብት ከጥግ እስከ ጥግ እንዲከበርና ጥበቃ እንዲያገኝ እንዲደረግ ስለመጠየቅ ነው። በዚህ ወረቀት እንደቀረበው ይህ መሆን የሚችለው ለሙጡ የመንግስት ለውጥ ብቻ ሳይሆን የስርዓትም ለውጥ ሲሆን ነው። በታሪክ እንደምናውቀው እውነተኛ የስርዓት ለውጥ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ደርግ በነበረው ሽግግር ብቻ ነው። ከደርግ ወደ ወያኔ የተደረገው ሽግግር የመግስት ለውጥ እንጂ የስርዓት ለውጥ የለበትም። ወያኔም ሆነ ደርግ ሁለቱም ኮምኒስቶችና አብዮታዊ ዲሞክራቶች ናቸው። ከወያኔ በኋላ በሚመጣው ለውጥ አንደኛና ሁለተኛ ዜግነት መሰረዝ ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ የመንግስት ለውጥ ብቻ ሳይሆን ለስርዓት ለውጥም ያስፈልጋል። በዚህ ለውጥ የስርዓት ለውጥ የግለሰብና የቡድን መብት እኩል የሚከበርበት፤ አንድ አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የግሰለብ መብት የአካባቢው የጎሳ መሪዎች የሚቸሯቸው ስጦታ ሳይሆን በዜግነታቸው ብቻ የሚያገኙት የማይሸራረፍ መብት ሆኖ መደንገግ ይኖርበታል።

4. ዛሬ ባገራችን እየሆነ ያለው ሁሉ ባለፉት አርባ ሁለት አመታት የመጣንበት የተሳሳተ መንገድ ውጤት ነው። ስለዚህ የተሰበረውን የሰላምና የእድገት ምሰሶ ለማቆም የተሸወድንባቸውን ያለፉት አርባ ሁለት አመታት በጥሞና መፈተሽ ይኖርብናል። ወደፊት በሚኖረው ሽግግር ወቅት ይህ ጉዳይ እንደ አንድ ትግል ፕሮዠ ተይዞ ከአጼው መውደቅ በኋላ የመጣንበት የቁልቁለት መንገድ ሊፈተሽ ይገባዋል። ኮምኒዝም በሚባለው ከውጭ የመጣ በሽታ ስንታመም አርባ ሁለት አመታት አባከንን። ከዚህ በሽታ ለመፈወስ በሀሰት ነጋሪዎች በውሸት የተከሰተባቸውን ያለፉት አርባ ሁለት አመታት በእውነት ላይ ተመስርተን ማከም አለብን።

ጹሁፌን ከማጠናቀቄ በፊት የገብረሕይዎት ባይከዳኝን አንድ ተጥይቅ ላንሳ። ገብረሕይዎት በመንግሥት እና የህዝብ አስተዳደር መፅሃፉ መቅድም ላይ እንዲህ ይላል፤

*«ሕዝቦችን ሁሉ የሚፈጥር አንድ አምላክ ነው። ይህም አምላክ የምንለው የሕዝቦች ፈጣሪ ሕዝቦችን ሁሉ ትክክል አንድ አድርጎ ፈጥሮ ላኗኗራቸውና ለልማታቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ከሙሉ ፈቃድና ስልጣን ጋር በእጃቸው ሰጥቷቸዋል። ስለዚህ ማናቸውም ህዝብ ቢለማም ቢጠፋም በገዛ እጁ ነው። ሕዝብ የሚጠፋበት አንዳንድ ምክንያት ቢያገኝ ያውም ምክንያት በአንዳንድ ሰው ቢመካኝ ትክክል አይደለም። የልማትን መንገድ ለማግኘት የሚጥር ሕዝብ ቢገኝ በአንዳንድ ክፉ ሰው ምክንያት ሊጠፋ አይችልም። እንዲሁም ደግሞ የልማትን መንገድ ለማግኘት የማይጣጣር ሕዝብ በአንዳንድ ደህና ሰው ኃይል ልማት ሊያገኝ አይችልም።»*

ይህ የገብረሕይዎት ተጠይቃዊ ሀሳብ ኢትዮጵያ ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለመመርመር ሲጠቀመን የሚችል ይመስለኛል።

ሁላችን ከተባበርን በወያኔ ተንኮል ብቻ ኢትዮጵያ አትፈርስም። እኛ እውነተኛ ራዕይና አላማ ኑሮን በጋራ ጉዳዮቻችን ዙሪያ በአንድነት ከቆምን በወያኔ ማኪያቬሌያዊ ጥበብ ብቻ የወያኔ ፍላጎት የሆነው የኢትዮጵያ መፍረስ ያለገደብ ሊፈጸም አይችልም። ስለዚህ መንፈሳዊ ወኔውን አግኝተን ራሳችንን መመርመር ከቻልን፤ እጣ ፋንታችን የተሳሰረ መሆኑን ተገንዝበን በአንድ ጉዳይ ሁለት አቋም፤ በሁለት ጎራ የተከፈለ አተያይ መያዛችን የጋራ ጉዳት መሆኑን ከተገነዘብን፤ እንደ ሱልጣን አሊሚራህ «የኢትዮጵያ ኃይሏ አንድነቷ ነው» ብለን የምናምን ከሆነ ኢትዮጵያን አሁን ካላችበት አደጋ ማውጣት ብቻ ሳይሆን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ሁልጊዜ እንደሚሉት የምንመካባትና የምንኮራባት አገር ልናረጋት ችሎታው አለን፤ ይህንን የማድረግ ፈቃደኝነቱ ካለን ጊዜ ሳንወስድ አሁኑኑ መጀመር አለብን።

አመሰግናለሁ!